# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች - ሁለተኛ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

የዚህ መልእክት ጸሐፊ ጳውሎስ ነው (1፥1፣ 10፥1 ይመ)፡፡ መልእክቱ የጳውሎስ የአጻጻፍ ስልት ጐልቶ የሚታይበት ሲሆን፣ ከሌሎች መልእክቶቹ ይልቅ በዚህኛው ሰፋ ያለ ነገር ስለ ራሱ ተጽፎ እናገኛለን፡፡

### የተጻፈበት ጊዜ

መልእክቱ የተጻፈበት ዘመን ከሞላ ጐደል 55 ዓ.ም. ገደማ መሆኑን የተገኙት ማስረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከ1ኛ ቆሮ 16፥5-8 እንደምንረዳው የመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት የተጻፈው ከበዓለ ኀምሳ በፊት በኤፌሶን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የተጻፈው ከዚያ በኋላ ዋናው ክረምት ከመግባቱ በፊት በዚያኑ ዓመት ነው፡፡ መልእክቱ የተጻፈው በመቄዶንያ መሆኑን ከ2ቆሮ 2፥13፣ 7፥5 መረዳት ይቻላል፡፡

### የመልእክቱ ተደራስያን

የመልእክቱ መክፈቻ ሰላምታ መልእክቱ በቆሮንቶስ ላለችው ቤተ ክርስቲያንና በአካይያ ለሚገኙ ክርስቲያኖች የተጻፈ መሆኑን ያስረዳል (1፥1)፡፡ አካይያ ከመቄዶንያ በስተ ደቡብ ያለውን የግሪክ አገር በሙሉ የሚያጠቃልል፣ የሮማ መንግሥት ግዛት አንድ አውራጃ ነበረች፡፡

### የመልእክቱ ዐላማ

የጳውሎስን ክብር የሚነኩና ሐዋርያዊ ሥልጣኑን የሚቀናቀኑ ሐሰተኞች መምህራን፣ ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሠርገው ገብተው ነበር፡፡ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሁለት አጫጭር ጒብኝት አደርጋለሁ ካለ በኋላ፣ መልሶ አንድ ጊዜ ብቻ የረጅም ጊዜ ጒብኝት እንደሚያደርግ በመናገሩ፣ ጠላቶቹ ቃሉን የማይጠብቅ ሰው ነው በማለት አስወርተውበታል፡፡ ከዚህም ሌላ ጳውሎስ እውነተኛ ሐዋርያ አለመሆኑንና በኢየሩሳሌም ለነበሩ ድኾች የተሰበሰበውን የርዳታ ገንዘብ ለራሱ ጥቅም ያውላል እያሉ ስሙን ያጠፉ ነበር፡፡ እርሱ ግን ከቆሮንቶስ ምእመናን ጋር በቈየበት ጊዜ ሁሉ ሕይወቱ ምን ይመስል እንደ ነበርና ከአንደበቱ ይሰማ የነበረውም የድነት መልእክት ትክክለኛ መልእክት መሆኑን እንዲያስታውሱ ያሳስባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከአንድ ዓመት በፊት ለችግረኞቹ ወገኖች ማሰባሰብ የጀመሩትን ርዳታ እያጠናቀቁና በመካከላቸው ካሉት ሁከት ፈጣሪዎች እየተጠነቀቀ እርሱ ወደ እነርሱ በሚመጣበት ጊዜ፣ ዝግጁ ሆነው እንዲጠብቁት አጥብቆ ይለምናቸዋል፡፡ የጻፈላቸውም በቅንነት መንፈስ መሆኑን እንዲረዱላት ያስጠነቅቃቸዋል፡፡

### ውቅሩ

የመልእክቱ የጽሑፍ አወቃቀር ጳውሎስ ወደ ፊት ለሦስተኛ ጊዜ በቆሮንቶስ ሊያደርግ ከፈለገው ጒብኝት ጋር የተያያዘ ነው፤ መልእክቱ በሦስት ይከፈላል:-

1. ጳውሎስ የጒብኝቱን ዕቅድ የሠረዘበትን ምክንያት ያስረዳል (ም 1-7)፤
2. የቆሮንቶስ ሰዎች በመዋጮው ላይ ገንዘብ ማሰባሰቡን አጠናቀው ዝግጁ ሆነው እንዲጠብቁት ያበረታታቸዋል (ም8-9)፤
3. ጳውሎስ ወደ እነርሱ የመምጣቱን እርግጠኛነት፣ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑንና ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን ደግሞ አስፈላጊውን የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዐት ለማስከበር እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ መሆኑን ይገልጽላቸዋል (ም10-13)፡፡

### የመልእክቱ ወጥነት

የመልእክቱ ሐሳብ የተያያዘ አይደለም የሚሉ አሉ (የ2፥3-4 ማብ ይመ)፡፡ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው የጽሑፉ አወቃቀር እንደሚያስረዳው የመልእክቱ ሐሳብ ወጥ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት መጽሐፉ አሁን ባለው መልኩ ወጥ ሐሳብ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለምሳሌ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ መልእክቱን የሚያውቁት በዚሁ መልኩ ነበር፡፡ ከዚህም በላይ ጥንታውያን የግሪክ ቅጆች መጽሐፉን ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከፍለውት አያውቁም፡፡

### አስተዋፅኦ

1. ጳውሎስ ስለ ራሱ ሥነ ምግባርና ስለ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ ያብራራበት ዐቂቦተ እምነት (ም1-7)

   ሀ. ሰላምታ (1፥1-2)
   
   ለ. በመከራ ጊዜ መጽናኛ ለሆነው አምላክ ምስጋና (1፥3-11)
   
   ሐ. የጳውሎስ ዐላማና ባሕርይ ትክክለኛ መሆኑ (1፥12-2፥4)

መ. በቆሮንቶስ የነበረው በደለኛ ይቅር መባሉ (2፥5-11)
ሠ. በአገልግሎት የእግዚአብሔርን ምሪት መቀበል (2፥12-17)
ረ. የቆሮንቶስ ምእመናን ከክርስቶስ እንደ ተላከ መልእክት መቍጠራቸው (3፥1-11)
ሰ. የእግዚአብሔርን ክብር ባለተሸፈነ ፊት ማየት (3፥12-4፥6)
ሸ. በሸክላ ዕቃ ውስጥ የተቀመጠ ክቡር ነገር (4፥7-16ሀ)
ቀ. የሞት አይቀሬነትና ለክርስቲያን የሚሰጠው ትርጒም (4፥16ለ-5፥10)
በ. የማስታረቅ አገልግሎት (5፥11-6፥10)
ተ. አንድ መንፈሳዊ አባት ለልጆቹ ያለው ቀረቤታ (6፥11-7፥4)
ቸ. ከቲቶ ጋር መገናኘት (7፥5-16)

2. በኢየሩሳሌም ለነበሩ ክርስቲያኖች ርዳታ እንዲሰበሰብ ጥብቅ ማሳሰቢያ መስጠቱ (ም8፥8-9)

ሀ. ቸርነት ሲበረታታ (8፥1-15)
ለ. ቲቶና ባልንጀሮቹ ወደ ቆሮንቶስ መላካቸው (8፥16-9፥5)
ሐ. በልግስና መስጠትና ውጤቱ (9፥6-15)

3. ጳውሎስ ስለ ሐዋርያዊ ሥልጣኑ ትክክለኛነት ለማሳመን ሙግት መግጠሙ (ም10-13)

ሀ. ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣኑንና የአገልግሎቱን ክልል ከተቃዋሚዎቹ መከላከሉ (ም10)
ለ. ጳውሎስ አስፈላጊ ወዳልሆነ ትምክሕት እንዲገባ መገፋፋቱ (ም11-12)
ሐ. የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ (13፥1-10)
መ. መደምደሚያ (13፥11-14)

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፣ ከወንድማ
ችንም ከጢሞቴዎስ፤

በቆሮንቶስ ላለችው ለእግዚአብሔር ቤተ ክር
ስቲያን እንዲሁም በመላው አካይያ ለሚ
ኖሩ ቅዱሳን ሁሉ፤

2ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢየ
ሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

### የመጽናናት አምላክ

3የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ አም
ላክ የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አምላክና አባት ይባረክ። 4እኛ ራሳችን ከእግዚ
አብሔር በተቀበልነው መጽናናት፣ በመከራ
ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣ እርሱ በመ
ከራችን ሁሉ ያጽናናል። 5የክርስቶስ ሥቃይ
በእኛ ላይ የመብዛቱን ያህል መጽናናታች
ንም በክርስቶስ በኩል ይበዛልናል። 6መከራ
ብንቀበል ስለ እናንተ መጽናናትና መዳን
ነው። ብንጽናናም እኛ የተቀበልነውን መከራ
በመቀበል በትዕግሥት እንድትጸኑ ስለ እና
ንተ መጽናናት ነው። 7ስለ እናንተ ያለን
ተስፋ ጽኑ ነው፤ ምክንያቱም በመከራችን
እንደ ተካፈላችሁ ሁሉ በመጽናናታችንም
እንደምትካፈሉ እናውቃለን።
8ወንድሞች ሆይ፤ በእስያ ስለ ደረሰብን
መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በሕይወት
ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ
ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶ
ብን ነበር። 9በእርግጥም የሞት ፍርድ እንደ
ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው
ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድ
ንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን
ነው። 10እርሱ እንዲህ ካለው የሞት አደጋ
አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ወደ ፊትም ደግሞ
እንደሚያድነን ተስፋችንን በእርሱ ላይ ጥለ
ናል። 11እናንተም በጸሎታችሁ ደግፉን፤ በብ
ዙዎች ጸሎት ስለ ተሰጠን ስጦታ ብዙ ሰዎች
ስለ እኛ[ሀ] ምስጋና ያቀርባሉ።

### ጳውሎስ ዕቅዱን ለወጠ

12እንግዲህ ትምክህታችን ይህ ነው፤ በዚህ
ዓለም በተለይም ከእናንተ ጋር ባለን ግን
ኙነት፣ ከእግዚአብሔር በሆነ ቅድስናና ቅንነት
እንደኖርን ኅሊናችን ይመሰክራል፤ ይህም
በሰው ጥበብ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ነው።
13ልታነቡት ወይም ልትረዱት የማትችሉ
ትን ነገር አንጽፍላችሁም፤ ሁሉንም እንደም
ትረዱ ተስፋ አደርጋለሁ። 14እናንተ በእኛ
እንደምትመኩ ሁሉ እኛም በእናንተ እንደ
ምንመካ አሁን የተረዳችሁን በከፊል ቢሆ
ንም፣ በጌታ ኢየሱስ ቀን ሁሉን ትረዳላ
ችሁ።
15በዚህ እርግጠኛ ስለ ነበርሁ በዕጥፍ እን
ድትጠቀሙ፣ በመጀመሪያ ልጐበኛችሁ ዐቅጄ
ነበር። 16ወደ መቄዶንያ ስሄድ እግረ መንገ
ዴን ልጐበኛችሁና ከመቄዶንያም በእና
ንተ በኩል ተመልሼ ወደ ይሁዳ ስሄድ በጕ
ዞዬ እንድትረዱኝ ዐቅጄ ነበር። 17ይህን
ሳቅድ በሚገባ ሳላስብ ያደረግሁት ይመስላ
ችኋልን? ወይስ በዓለማዊ ልማድ እንዴ፣

[ሀ]11 ብዙ ቅጆች እናንተ ይላሉ

1፥1 ሐ16፥1፤18፥1፡12፤1ቆሮ1፥1፤10፥32፤ኤፌ1፥1፤10፥32፤ ኤፌ1፥1፤ቈላ1፥1፤ 2ጢሞ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ኤፌ1፥3፤1ጴጥ 1፥3
1፥4ኢሳ49፥13፤51፥12 ፤66፥13፤2ቆሮ 7፥6፡7፡13
1፥5 ሮሜ8፥17፤ 2ቆሮ4፥10፤ገላ6፥17፤ ፊል3፥10፤ቈላ1፥24፤ 1ጴጥ4፥13
1፥6 2ቆሮ4፥15
1፥7 ቍ5
1፥8 ሐሥ2፥9፤ሮሜ 11፥25፤1ቆሮ15፥32
1፥9 ኤር17፥5፡7፤ ዮሐ5፥21
1፥10 ሮሜ15፥31፤ 1ጢሞ4፥10
1፥11 ሮሜ15፥30፤ 2ቆሮ4፥15፤9፥11፤ፊል 1፥19
1፥12 ሐሥ23፥1፤ 1ቆሮ1፥17፤2፥1፡4፡13 2ቆሮ2፥17፤1ተሰ2፥10
1፥14 1ቆሮ1፥8
1፥15 ሮሜ1፥11፡13 ፤15፥29፤1ቆሮ4፥19
1፥16 ሐሥ16፥9፤ 19፥21፤1ቆሮ16፥5-7 ፡11፤3ዮሐ6
1፥17 2ቆሮ10፥2፡3 ፤11፥18

1፥1 *ሐዋርያ፤* ለተለየ ተልእኮ በክርስቶስ የተሾመ ነው (የማር6፥30፤ የ1ቆሮ 1፥1፤ የዕብ 3፥1 ማብ ይመ)። *ከወንድማች ንም፤* በክርስቶስ ወንድማችን ማለቱ ነው (ከሐሥ 9፥17፤ ዕብ 2፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። *ከጢሞቴዎስ፤* ይህ መልእክት በተጻፈበት ወቅት ከጳውሎስ ጋር ነበር፤ ሆኖም መልእክቱን ከጳውሎስ ጋር ጽፎአል ማለት አይቻልም። *ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፤* የአማኞች ኅብረት ስትሆን ሁሉን ዐቀፍ የሆነችውን ቤተ ክርስ ቲያን በዚህ ምድር የምትወክል ናት (የ1ቆሮ 1፥2 ማብ ይመ)። *ቅዱሳን፤* ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጠ ሌላ ስያሜ ሲሆን፣ "ለጌታ የተቀደሱና የተለዩ" ማለት ነው (የሮሜ 1፥7 ማብ ይመ)። *አካይያ፤* የግሪክ አገር ነው፤ ይህም በስተ ሰሜን በኩል የሚገኘ ውን መቄዶንያን አይጨምርም። መልእክቱ በቆሮንቶስ በነበረው ሁኔታ ላይ ያተኰረ ቢሆንም፣ በግሪክ አገር ሁሉ ለሚገኙ ክርስቲያኖችም ታስቦ የተጻፈ ነው። የመልእክቱ ቅጅ በቆሮንቶስ ከተዘጋጀ በኋላ፣ በአካይያ የነበሩ አማኞችም እንዲያነቡት ተልኮ ላቸው ሊሆን ይችላል።

1፥2 *ጸጋና ሰላም፤* የዮና 4፥2፤ ዮሐ 14፥27፤ 20፥19፤ ገላ 1፥3፤ ኤፌ 1፥2 ማብ ይመ።

1፥3 *የመጽናናትም፤* በሐዘን ውስጥ ላለ ሰው የሚሰጥ ማበ ረታቻ ነው፤ አማኞች ስለ ኢየሱስ መከራ በሚቀበሉበት ጊዜ እን ዲህ ዐይነቱን መጽናናት ያገኛሉ፤ ይህም በመከራ ላይ የሚገኙትን ሌሎች ሰዎች ለማጽናናት ብቁ ያደርጋቸዋል (ቍ 4-7)። *አምላክ፤* የመጽናናታችን ምንጭ ነው።

1፥8 *ስለ ደረሰብን መከራ፤* ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ በአንደኛ መደብ ብዙ ቍጥር ማለትም፣ "እኛ" እያለ ይጽፋል። በግልጽ ካልተነገረ በስተቀር እንዲህ ዐይነቱ አገላለጽ የሚያመ ለክተው ጳውሎስን ብቻ ነው። *በእስያ፤* በትንሿ እስያ በስተ ምዕራብ የነበረ የሮማውያን ክፍለ ግዛት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በቱ ርክ ግዛት ውስጥ ይገኛል። ጳውሎስ መከራ የተቀበለበት ስፍራም ሆነ የመከራውም ዐይነት በትክክል አልተገለጸም።

*1፥9፤* ጳውሎስ የደረሰበት መከራ ለሕይወቱ እጅግ አሥጊ ስለ ነበር፣ ከዚያ ሁሉ መትረፉን የሚያየው ከሞት የመነሣት ያህል አድርጎ ነበር። *በእግዚአብሔር እንድንታመን፤* የዚህ መልእክት ዐቢይ መርሕ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉን ያስች ላል፤ ድካማችን ደግሞ ኀይሉ እንዲገለጥ ያደርጋል (ከ12፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

*1፥12፤* ጳውሎስ ስሙን ለማጥፋት የተከፈተበትን የወሬ ዘመቻ ለመከላከል፣ የገዛ ኅሊናውንና ማንነቱን በሚገባ የሚያውቁ ትን የቆሮንቶስን ሰዎች ምስክር አድርጎ ይጠራል። በመጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ ዐሥራ ስምንት ወር ያህል ከእነርሱ ጋር ቈይቶአል (ሐሥ 18፥11)፤ ስለዚህ ጨዋነቱን ሊክዱ አይች ሉም።

*1፥13፤* የጳውሎስን ማንነት በሚገባ ስለሚያውቁ፣ የትም ሆኖ የሚጽፍላቸውን ነገር በእምነት ይቀበሉታል፤ ምክንያቱም ጳውሎስ ለሚናገረው ነገር ሁሉ እውነተኛና ታማኝ ነው።

1፥14 *በከፊል፤* አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች በጳውሎስና በሐዋርያዊ ሥልጣኑ ላይ የነበራቸው እምነት፣ ሠርገው በገቡ ሐሰ ተኞች ሐዋርያት እንዲናጋ አድርገዋል። *በጌታ ኢየሱስ ቀን፤* በዳግም ምጽአቱ ነው (ከ1ተሰ 2፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥15 *በዕጥፍ እንድትጠቀሙ፤* ጳውሎስ በዚህና በቍ 16 ላይ ስለ ጕዞው ዕቅድ መቀየር ይናገራል። በመጀመሪያ የነበ ረው ዕቅድ በሰሜን በኩል ወደ መቄዶንያ ከመሄዱ በፊት ከኤፌሶን በቀጥታ ባሕሩን አቋርጦ ወደ ቆሮንቶስ በመሄድ ሊጐበ ኛቸውና ከመቄዶንያ ሲመለስ ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ሊጐበኛቸው ነበር፤ በዚህ መሠረት ለአጭር ቈይታ ሁለት ጊዜ ቢጐበኛቸው ይጠቅማቸው ነበር። ይህ እንግዲህ ከቆሮንቶስ ሰዎች ጋር ሆድና ጀርባ ከመሆናቸው በፊት ነበር። ይሁን እንጂ ከኤፌሶን በቀጥታ ወደ ቆሮንቶስ በመሄድ ያልታሰበ ጕዞ በማድረግ ሳይጐበኛቸው አይቀርም፤ ይህም እጅግ "ያዘኑበት" (2፥1) ጕብኝት ነበር። የሚ ያሳዝን መልእክት እንዲጽፍላቸው ያበቃውም ይኸው ጕብኝት ነበር (7፥8-9 ይመ)።

1፥17 *በሚገባ ሳላስብ ያደረግሁት፤* ጳውሎስ ዕቅዱን ሲለ ውጥ ያዩ በቆሮንቶስ የነበሩ ተቃዋሚዎቹ በቃሉ የማይታመንና ተስፋ የማይጣልበት ሰው እንደሆነ በመናገር፣ በዚያ የነበሩ ክርስ ቲያኖችን ለማሳመን ይጥሩ ነበር። ጳውሎስ እነዚህን ሁለት

"አዎን፣ አዎን" ወዲያው ደግሞ፣ "አይደለም፣
አይደለም" የምል ይመስላችኋልን?
18እግዚአብሔር ታማኝ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ለእ
ናንተ የምንናገረው ቃላችን፣ "አዎን" እና "አይ
ደለም" ሊሆን አይችልም፤ 19ምክንያቱም
እኔም ሆንሁ ሲላስና[a] ጢሞቴዎስ፣ እኛ የሰ
በክንላችሁ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ "አዎን" እና "አይደለም" አልነበረም፤
ነገር ግን በእርሱ ዘወትር፣ "አዎን" ነው።
20ከእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣ "አዎን"
የሚሆኑት በእርሱ ነውና፤ እኛም በእርሱ አማ
ካይነት ለእግዚአብሔር ክብር፣ "አሜን" የምን
ለው በዚህ ምክንያት ነው። 21እንግዲህ፣
እኛንም እናንተንም በክርስቶስ ጸንተን እን
ድንቆም የሚያደርገን እግዚአብሔር ነው፤
የቀባንም እርሱ ነው፤ 22የእርሱ ለመሆናችን
ማኅተሙን ያተመብን ደግሞም ወደ ፊት
ለምናገኘው ነገር የመንፈሱን ዋስትና በልባ
ችን ያኖረ እርሱ ነው።
23ወደ ቆሮንቶስ ተመልሼ ያልመጣሁት
እንዳላሳዝናችሁ ብዬ ነው፤ ይህ እውነት
ካልሆነ እግዚአብሔር ይመስክርብኝ። 24ጸንታ
ችሁ የምትቆሙት በእምነት ስለ ሆነ፣ ደስ
እንዲላችሁ ከእናንተ ጋር እንሠራለን እንጂ
በእምነታችሁ ላይ ለመሠልጠን አይደለም።
2 እንግዲህ ላሳዝናችሁ ስላልፈለግሁ ወደ
እናንተ ዳግመኛ ላለመምጣት ወሰንሁ፤
2እኔ ባሳዝናችሁም እንኳ፣ ከእናንተው ካሳዘ
ንኋችሁ በቀር ደስ የሚያሰኘኝ ማን አለ?
3ባለፈው ጊዜ እንደዚያ የጻፍሁላችሁ ወደ
እናንተ ስመጣ ደስ ሊያሰኙኝ የሚገባቸው
ሰዎች እንዳያሳዝኑኝ በማለት ነው፤ ምክን
ያቱም የእኔ ደስታ የሁላችሁ ደስታ እንደ
ሚሆን አምናለሁ። 4እንደዚያ ስጽፍላችሁ
በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት፣ በብዙም
እንባ ውስጥ ነበርሁ፤ ይህንንም ያደረግሁት
ለእናንተ ያለኝን ጽኑ ፍቅር እንድታውቁ በማ
ለት እንጂ፣ እናንተን ለማሳዘን አልነበረም።

## በደለኛን ይቅር ማለት

5ማንም ሰውን ቢያሳዝን፣ ነገር ማጋነን
አይሁንብኝና ያሳዘነው እኔን ብቻ ሳይሆን
በመጠኑም ቢሆን ሁላችሁንም ነው። 6እን
ደዚህ ያለው ሰው ብዙዎች የወሰኑበት ቅጣት
በቂው ነው። 7ደግሞም ከልክ በላይ አዝኖ
ተስፋ እንዳይቈርጥ፣ ይቅር ልትሉትና ልታ
ጽናኑት ይገባችኋል። 8ስለዚህ አሁንም የም
ትወዱት መሆናችሁን እንድትገልጹለት እለ
ምናችኋለሁ። 9የጻፍሁላችሁም፣ የሚያጋጥማ
ችሁን ፈተና መቋቋማችሁንና በሁሉም ነገር
ታዛዦች መሆናችሁን ለማወቅ ነበር። 10እና
ንተ ይቅር የምትሉትን ሰው እኔም ይቅር
እለዋለሁ፤ በእርግጥ ይቅር የምለው ነገር
ካለ፣ በክርስቶስ ፊት ይቅር የምለው ስለ
እናንተ ስል ነው። 11ይህንንም የምናደርገው
ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝ ነው፤ የእ
ርሱን ዕቅድ አንስተውምና።

## የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች

12የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ወደ ጢሮ
አዳ በሄድሁ ጊዜ፣ ጌታ በር ከፍቶልኝ ነበር፤

[a]19 ግሪኩ *ሲልዋኖስ* ይላል

1፥18 1ቆሮ1፥9
1፥19 ማቴ4፥3፤ ሐሥ 15፥22፤16፥1፤ ዕብ13፥8
1፥20 ሮሜ15፥8:9 ፤1ቆሮ14፥16
1፥21 1ቆሮ16፥13፤ 1ዮሐ2፥20:27
1፥22 ዘፍ38፥18፤ ሕዝ9፥4፤ሐጌ2፥23፤ 2ቆሮ5፥5
1፥23 ሮሜ1፥9፤ 1ቆሮ4፥21፤2ቆሮ2፥1 :3፤13፥2:10
1፥24 ሮሜ11፥20፤ 1ቆሮ15፥1፤1ጴጥ5፥3
2፥1 2ቆሮ1፥23
2፥2 2ቆሮ7፥8
2፥3 ቆላ4:9፤2ቆሮ 7፥8:12:16፤8፥22፤12 ፥21፤ገላ5፥10፤2ተሰ3፥ 4፤ፊሞ21
2፥4 ቆላ3:9፤2ቆሮ 7፥8:12
2፥5 1ቆሮ5፥1:2
2፥6 1ቆሮ5፥4:5፤ 2ቆሮ7፥11
2፥7 ገላ6፥1፤ኤፌ 4፥32፤ቈላ3፥13
2፥9 ቆላ3:4፤2ቆሮ 7፥8:12:15፤10፥6
2፥11 ማቴ4፥10፤ ሉቃ22፥31፤2ቆሮ4፥4 ፤1ጴጥ5፥8:9
2፥12 ሐሥ14፥27፤ 16፥28፤ሮሜ1፥1፤ 2ቆሮ4፥3:4፤8፥18፤9፥ 13፤1ተሰ3፥2፤ቲቶ1፥4

ጥያቄዎች ያቀረበው በሚገባ ሳያስብ የሚናገርና ሐሳቡም የማ ይጨበጥ ሰው አለመሆኑን ለመግለጽ ነው። ያም ሆነ ይህ ጳው ሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን ለመጐብኘት የነበረውን ዕቅድ ቀየረ እንጂ ጨርሶ አልተወም።

1፥18 *"አዎን" እና "አይደለም" ሊሆን አይችልም፤* ጳውሎስ እዚህ ላይ (ቍ 18-20) ቀደም ሲል ስለ ሰበከላቸው የወንጌል መልእክት ያሳስባቸዋል፤ ይኸውም የተቀበሉት ወንጌል ፍጹም እውነትና አሻሚነት የሌለው መሆኑን ተረድተዋል፤ ደግሞም ታላቅ ኀይል ያለውን ሥራውን በሕይወታቸው በማየታቸው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል፣ "አዎን" የሚሆነው በክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ አረጋግጠዋል።

1፥20 *"አሜን"፤* ይህ "አሜን" ምእመናን ጸሎት ወይም ምስጋና አቅርበው እንደጨረሱ የሚሉት ነው (ከ1ቆሮ 14፥16 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥22 *ማኅተሙን፤* የሐጌ 2፥23 ማብ ይመ። *ዋስትናን፤* ሙሉው ወደፊት እንደሚሰጥ ለማረጋገጥ ለጊዜው በከፊል የሚሰጥ ነው። አሁን በከፊል የሚሰጠው የሙሉው አካል ነው።

1፥23 *እንዳላሳዝናችሁ ብዬ፤* ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ለመጐብኘት የነበረውን ዕቅድ የቀየረው ከፍቅርና ለእነርሱ ከማሰብ የተነሣ እንጂ፣ ከወላዋይነትና ከግድ የለሽነት የተነሣ አልነበረም።

2፥1 *ላሳዝናችሁ ... ዳግመኛ ላለመምጣት፤* ጳውሎስ ከዚህ ቀደም ጉብኝት ባደረገበት ወቅት የቆሮንቶስ ሰዎች አዝነው ነበር፤ አስፈላጊ ሆኖ ቢያገኘው ኖሮ ወደ እነርሱ ሄዶ ሊገሥጻቸው ቢችልም (ከ13፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፣ እንዲህ ዐይነቱን ጉብኝት መድገም አልፈለገም። ከዚህ በፊት ያደረገው ጉብኝት መቼ እንደ ሆነ አይታወቅም። ይህ ጉብኝት ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቆሮንቶስ በሄደበትና ወንጌልን ሰብኮ ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ጊዜ ሊሆን አይችልም። እንግዲህ ከ12፥14፤13፥1 እንደምንረዳው ወደ ቆሮንቶስ ሁለት ጊዜ ሄዷል ማለት ነው፤ ደግሞም በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ሊያደርግ ያሰበው ጉብኝት ሦስተኛው እንደ ሆነ ገልጾአል። ሁለተኛው ጉብኝት የተደረገው በመጀመሪያውና በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክቶች መጻፍ መካከል ሳይሆን አይቀርም፤ አንዳንዶች ግን የመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት ከመጻፉ በፊት እንደ ሆነ ይናገራሉ።

2፥3-4 *እንደዚያ የጻፍሁላችሁ ... በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት፤* ይህ ክፍል የሚያወሳው ከዚህ በፊት ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለተጻፈላቸው ደብዳቤ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ እንደ ተስማማችበት ከሆነ ይህ ደብዳቤ የመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት ነው። ይሁን እንጂ 1ኛ ቆሮንቶስ ከተጻፈ በኋላና 2ኛ ቆሮንቶስ ከመጻፉ በፊት ሌላ መልእክት ተጽፏል የሚለው ግምት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ተቀባይነት እያገኘ መጥቶአል። አንዳንድ የዚህ አመለካከት አራማጆች እንደሚሉት ይህ አወዛጋቢ ደብዳቤ ጠፍቶአል፤ ሌሎች ደግሞ ይህ ደብዳቤ በሙሉ ወይም በከፊል የዚሁ የ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክት የመጨረሻዎቹ አራት ምዕራፎች ናቸው ይላሉ፤ ለዚህም የሚያቀርቡት ማስረጃ እነዚህ አራት ምዕራፎች ከመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች ጋር ስሙም ካለመሆናቸውም በላይ መልእክቱ የተጻፈው፣ "በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት" ነው ከሚለው ሐሳብ ጋር ይጣጣማሉ በማለት ነው። ይሁን እንጂ የ2ኛቆሮንቶስ መልእክት ይዘት ወጥነት አጠያያቂ የሆነበት ወይም እስከዚህ ዘመን ድረስ የመልእክቱ ትክክለኛነት አጠራጣሪ የሆነበት ታሪካዊ ማስረጃ የለም።

*2፥5-11፤* ይህ ክፍል የሚናገረው በቆሮንቶስ አስከፊ በደል በመፈጸሙ ቤተ ክርስቲያን ቅጣት ስለ ወሰነችበት ስለ አንድ ግለሰብ ነው። ይህ በደል የፈጸመው ሰው በኀጢአቱ ተጸጽቶ ከልቡ ንስሓ ከገባ፣ የወሰኑበትን ቅጣት ማንሣትና ወደ ቀድሞው ኅብረት በፍቅር መመለስ እንዳለባቸው ጳውሎስ ያሳስባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በበደለኞች ላይ የምትወስነው ቅጣት ጠቃሚ ቢሆንም፣ ለይቅርታና ለምሕረት ስፍራ እስከማይገኝ ድረስ ርኅራኄና ፍቅር ማጣት የለባትም። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው በደል የተፈጸመው ጳውሎስ በመጀመሪያውና በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክት መጻፍ መካከል ወደ ቆሮንቶስ በሄደበት ጊዜ ሊሆን ይችላል (የቍ 1 ማብ ይመ)፤ በደለኛውም እንዲቀጣ ብርቱ ደብዳቤ የጻፈውም በዚሁ ምክንያት ነበር (የቍ 3-4 ማብ ይመ)። ከዚህ ሌላ በ1ቆሮ5 ላይ የተጻፈውን በደል ያመለክታል የሚልም አመለካከት አለ።

2፥12 *ወደ ጢሮአዳ በሄድሁ ጊዜ፤* ጳውሎስ ከኤፌሶን ተነሥቶ ቴኔደስ ደሴት ትይዩ በኤጂያን ባሕር ጠረፍ ላይ ወደምት

13ይሁን እንጂ ወንድሜን ቲቶን እዚያ ስላ
ላገኘሁት መንፈሴ አላረፈም፤ ስለዚህ ተሰና
ብቻቸው ወደ መቄዶንያ ሄድሁ።
14ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል
አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን፣ የዕውቀቱ
ንም መዐዛ በእኛ አማካይነት በየስፍራው
ለሚገልጥ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤ 15ምክን
ያቱም በሚድኑትና በሚጠፉት መካከል ለእ
ግዚአብሔር የክርስቶስ መዐዛ ነን። 16ለሚጠፉት
ወደ ሞት የሚወስድ የሞት ሽታ፣ ለሚድኑት
ግን ወደ ሕይወት የሚወስድ የሕይወት
ሽታ ነን፤ ታዲያ፣ ለዚህ ብቁ የሚሆን ማን
ነው? 17እኛኮ ትርፍ ለማግኘት ብለን የእግዚ
አብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት
እንደ ብዙዎቹ አይደለንም፤ ነገር ግን ከእግ
ዚአብሔር እንደተላኩ ሰዎች በክርስቶስ ሆነን
በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን።

2፥13 ሐሥ16፥9፤ 2ቆሮ 7፥5፡6፡13፤8፥6፡16፡23፤12፥18፤ገላ2፥1፡3፤ቲቶ1፥4
2፥14 ሕዝ20፥41፤ ሮሜ6፥17፤7፥25፤ 1ቆሮ15፥57፤2ቆሮ8፥7፤2ቆሮ9፥15፤ኤፌ5፥2፤ፊል4፥18
2፥15 ቍ14፤ዘፍ 8፥21፤ዘፀ29፥18፤ዘኍ15፥3፤1ቆሮ1፥18
2፥16 ሉቃ2፥34፤ ዮሐ3፥36፤2ቆሮ3፥5፡6
2፥17 ሐሥ20፥33፤ 1ቆሮ5፥8፤2ቆሮ1፥12፤4፥2፤12፥19፤1ተሰ2፥5
3፥1 ሐሥ18፥21፤ ሮሜ16፥1፤1ቆሮ16፥3፤2ቆሮ5፥12፤10፥12፡18፤12፥11
3፥2 1ቆሮ9፥2
3፥3 ቍ7፤ዘፀ24፥12፤31፥18፤32፥15፡16፤ምሳ3፥3፤7፥3፤ኤር31፥33፤ሕዝ36፥26፤ማቴ16፥16 3፥4 ኤፌ3፥12 3፥5 1ቆሮ15፥10፤ 2ቆሮ2፥16
3፥6 ሉቃ22፥20፤ ዮሐ6፥63፤ሮሜ2፥29፤7፥6

3እንደ ገና ራሳችንን ልናመሰግን እንጀም
ራለንን? ወይስ እንደ ሌሎቹ ለእናንተ
ወይም ከእናንተ የተጻፈ የምስጋና ደብዳቤ
ያስፈልገን ይሆንን? 2እናንተኮ ሰው ሁሉ
የሚያውቃችሁና የሚያነባችሁ በልባችን ላይ
የተጻፋችሁ ደብዳቤዎቻችን ናችሁ፤ 3እና
ንተ በቀለም ሳይሆን በሕያው እግዚአብሔር
መንፈስ፣ በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን በሰው
ልብ ጽላት ላይ የተጻፋችሁና በእኛ የተገለ
ገላችሁ የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤ ናችሁ።
4በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ላይ ያለን
እምነት ይህን የመሰለ ነው፤ 5ብቃታችን
ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፣ በራሳችን ብቃት
ከእኛ ነው የምንለው አንዳች ነገር የለንም።
6እርሱም በፊደል ላይ ሳይሆን በመንፈስ
ላይ የተመሠረተውን የአዲሱ ኪዳን አገልጋ
ዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን፤ ምክን

ገኘው ወደ ጢሮአዳ ከተማ ሄዶ ነበር፤ ወደዚያም የሄደው ቲቶን ለማግኘትና ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ለመጠየቅ ነበር። ቲቶ ግን ጳውሎስ ባሰበው መንገድ ወደ ጢሮአዳ አልመጣም፤ ስለዚህ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች የነበሩበትን ሁኔታ ለማወቅ እጅግ ስለ ጓጓ "ወደ መቄዶንያ ሄደ" (ቍ13)፤ የሄደውም ወደ ፊልጵስዩስ ከተማ ሳይሆን አይቀርም።

2፥13 *ወንድሜን፤* ከ8፥23 ጋር ያነጻጽሩ። ጳውሎስ ቲቶን ይወደውና ያከብረው ስለ ነበር፣ በኢየሩሳሌም የነበሩ ድኾች ክርስቲያኖችን ለመርዳት በቆሮንቶስ ገንዘብ የማሰባሰብ ኀላፊነት ሰጥቶት ነበር (8፥6)፤ ይህንንም መልእክት ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንዲያደርስ መርጦታል (8፥16-17)።

*2፥14፤* እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ጕዞው መተረኩን ትቶ ድንገት ወደ ሌላ ርእስ ጕዳይ ይገባል (የተወውን ሐሳብ እስከ 7፥5 ድረስ አያነሣም)። ይሁን እንጂ ወደ ሌላ ርእስ ጕዳይ መግባቱ ለዚህ ደብዳቤ የሐሳብ ፍሰት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ጳውሎስ የቱንም ያህል አስፈሪና አደገኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ቢያልፍም፣ በገጠመው ነገር ሁሉ ድልን በሚሰጠው በእግዚአብሔር ጸጋ ምስጋናውን ያቀርባል። *በድል አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን፤* ይህ ምሳሌ የተወሰደው ከሮማውያን የድል በዓል አከባበር ነው፤ አንድ የጦር አዛዥ በእልልታና በጭብጨባ ሊቀበለው በወጣው ሕዝብ ፊት ሰራዊቱንና የማረካቸውን ምርኮኞች እየመራ ሲገባ አየሩ በየመንገዱ ዳር በሚጤሰው መልካም መዐዛ ባለው ሽታ ይታወድ ነበር። እንደዚሁም ለመንፈሳዊ ውጊያ የተጠሩ ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት በድል አድራጊነት ይመራቸዋል፤ ደግሞም እግዚአብሔር የክርስቶስን የዕውቀት፣ "ሽታ" በየስፍራው የሚያሠራጨው በእርሱ በኩል ነው።

2፥16 *የሞት ሽታ ... የሕይወት ሽታ፤* ሰዎች ወንጌልን ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም በክርስቲያኖች ምስክርነት አማካይነት ለዓለም ሲታወጅ ዘወትር መልካም ሽታ አለው። ሰዎች በመጨረሻ፣ "በሚድኑትና በሚጠፉት" በሚለው ሁለት መደብ ይፈረጃሉ (ቍ15)። የምሥራች የሚነግሩ ክርስቲያኖች ለሚጠፉት የሞት ሽታ ይሆኑላቸዋል፤ እንዲህ ሲባል የወንጌል መልእክት ለሚያምኑት በውኑ መጥፎ ሽታ ሆኖ ሳይሆን፣ ሕይወት የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ባለመቀበላቸው ሞትን በራሳቸው ላይ ስለ ጋበዙ ነው፤ የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል በደስታ ለሚቀበሉ ሰዎች የምሥራቹን ቃል የሚነግሩ ክርስቲያኖች ግን የሕይወት ሽታ ይሆኑላቸዋል። ታዲያ ለዚህ ብቁ የሚሆን ማን ነው? ለመልሱ 3፥5 ይመ።

2፥17 *ትርፍ ለማግኘት ብለን የእግዚአብሔርን ቃል ... እንደሚሸቃቅጡት ... አይደለንም፤* ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሠርገው ስለ ገቡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ነው። እንደነዚህ ያሉ ቅንነት የሌላቸው፣ በራሳቸው የሚመኩና የሚታበዩ ሰዎች ብልጣ ብልጥ አቀራረብ አላቸው፤ ዐላማቸውም ከገራገር የቤተ ክርስቲያን አባላት ገንዘብ መንጠቅ ነው። በአንጻሩ ግን ጳውሎስ ወንጌልን ይሰብክ የነበረው በቅንነትና ያለ አንዳች ክፍያ ነበር፤ ይህንንም ያደረገው በገንዘብ ረገድ በቆሮንቶስ አማኞች ላይ ሸክም ላለመሆን አስቦ ነው (11፥7-12፤ 1ቆሮ 9፥7-15 ይመ)።

3፥1 *እንደ ገና ራሳችንን ልናመሰግን እንጀምራለንን?* ጳውሎስ የጻፈውን ወይም የተናገረውን ሁሉ በቆሮንቶስ የነበሩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሊያጣምሙትና ለክፋት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ሥጋቱን ይገልጻል። *የምስጋና ደብዳቤ፤* የሐዋርያትን ትምህርት እናስተምራለን የሚሉ አስመሳዮች ስለ ተነሡ፣ የምስጋና ደብዳቤ መያዝ አስፈላጊ ሆኖ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ዐይነቱ ማስረጃ አላስፈለገውም፤ የቆሮንቶስ ሠርጎ ገቦችን ጨምሮ ሌሎቹ ግን ማስረጃ መያዝ ያስፈልጋቸው ነበር፤ ሐሰተኞች 'በመሆናቸውም በተጭበረበረ መንገድ ወይም አስመስሎ በመሥራት የምስጋና ደብዳቤ ያዘጋጁ ነበር።

3፥2 *ሰው ሁሉ የሚያውቃችሁና የሚያነባችሁ፤* በተለወጠው ሕይወታቸው አማካይነት የወንጌል ኀይል ስለሚገለጥ ነው።

3፥3 *በቀለም ሳይሆን ... የተጻፋችሁና፤* በብዕርና ወይም በክርታስ ላይ እንደተጻፈ ጽሑፍ ሳይሆን ማለት ነው። *በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ፤* መንፈስ ቅዱስ መጻፊያ ቀለም ይመስል በዚህ መልክ ቀርቦአል። ቀለም ሕይወት የሌለው እንደመሆኑ ይደበዝዛል፤ በቀላሉም ይለቃል። የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ ግን ራሱ ሕይወት በመሆኑ ሕይወትን ይሰጣል (ቍ6)፤ የሚሰጠውም ሕይወት ዘላለማዊና እንከን የሌለበት ነው። *በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን፤* በሲና ተራራ ላይ እንደ ሆነው አይደለም (የቍ 6 ማብ ይመ)። *በሰው ልብ ጽላት ላይ፤* ኤር 31፥33፤ ሕዝ 11፥19፤ 36፥26 ይመ። ጳውሎስ በአሮጌውና በአዲሱ ኪዳናት መካከል ያለውን ንጽጽር በቍ7-18 ላይ ያብራራል። *የክርስቶስ ... ደብዳቤ፤* ጳውሎስ ጌታ የሚጠቀምበት መሣሪያ ብቻ ነው።

3፥5 *ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው፤* በ2፥16 ላይ፣ "ታዲያ ለዚህ ብቁ የሚሆን ማን ነው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ ነው።

3፥6 *የ ... አገልጋዮች፤* ለተልእኮአቸው የቆሙ ማለት ነው (ሮሜ15፥16፤ ቈላ1፥7፤4፥7፤ 1ጢሞ 4፥6 ይመ)። ጳውሎስ በ4፥1 ላይ፣ "ይህ አገልግሎት" ወደሚለው ጭብጥ ይመለሳል። *የአዲሱ ኪዳን፤* እዚህ ላይ ጳውሎስ፣ "በሰው ልብ ጽላት ላይ" (ቍ3) በማለት የጠቀሰውን ጭብጥ እንደ ገና ያነሣል። ዕብ ም8-10 እንዲሁም የዕብ 7፥22 ማብ ይመ። ጳውሎስ የአዲሱን ኪዳን አገልጋዮች "የሞት አገልግሎት" (ቍ7) ከሚለው ጋር ያነጻጸረው ክርስትናን በአይሁድ እምነት የሚበርዙ ተቃዋሚዎቹ በቆሮንቶስ ስለ ነበሩ ነው፤ ተቃዋሚዎቹም የጴጥሮስ ወገን ነን ሲሉ የነበሩና (1ቆሮ 1፥12) በ11፥22 ላይ ዕብራውያን የተባሉት ሊሆኑ ይችላሉ (የዚያኑ ማብ ይመ)። *ፊደል፤* ሕጉ በመጀመሪያ የተጻፈበት፣ "የድንጋይ ጽላት" ነው (ዘፀ24፥12፤31፥18፤32፥15-16 ይመ)። *መንፈስ፤* ሕጉን "በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ ... በልብ ጽላት ላይ" መጻፍ ሲሆን፣ ይህም በነቢያት የተነገረ የአዲሱ ኪዳን ተስፋ ነው (ኤር 31፥31-34፤ 32፥39-40፤ ሕዝ 11፥19፤ 36፥26 ይመ)። *ፊደል ይገድላል፤ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል፤* የመጽሐፍ ቅዱስ ውጫዊው ቃል በቃል ትርጕሙ የሚገድል፣ ውስጣዊው መንፈሳዊው የሚጠቅም ነው ማለት አይደለም። "ፊደል" ሕግ ተላላፊዎችን ከሚኰንነው ሕግ ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ስለዚህም፣ "የሞት አገልግሎት" እንዲሁም "ሰዎችን የሚኰንነው አገልግሎት" (ቍ7-9) ተብሎ ተገልጾአል። በሌላ በኩል ደግሞ ሕይወትን የሚሰጠው መንፈስ "የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ" ነው፤ እርሱም የአዲስ ኪዳን

ያቱም ፊደል ይገድላል፤ መንፈስ ግን ሕይ
ወትን ይሰጣል። 7እንግዲህ እስራኤላውያን
ከፊቱ ክብር የተነሣ የሙሴን ፊት ትኵር
ብለው ማየት እስኪሳናቸው ድረስ፣ ያ ከጊዜ
በኋላ የሚያልፈውና በድንጋይ ላይ በፊደል
የተቀረጸው የሞት አገልግሎት በክብር ከመጣ፣
8ታዲያ፣ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት
ከዚያ የላቀ ክብር አይኖረውም? 9ሰዎችን
የሚኰንነው አገልግሎት የከበረ ከሆነ፣ የሚያ
ጸድቀው አገልግሎት የቱን ያህል ይበልጥ
የከበረ ይሆን! 10ከዚህ በፊት ክቡር የነበረው
የላቀ ክብር ካለው ጋር ሲወዳደር ክብር
የሌለው ሆኖአል። 11የሚያልፈው ያን ያህል
ክብር ከነበረው፣ ጸንቶ የሚኖረውማ እን
ዴት የላቀ ክብር አይኖረውም?

12እንግዲህ ይህን የመሰለ ተስፋ ስላለን፣
በድፍረት እንናገራለን። 13እስራኤላውያን
የፊቱ ማንጸባረቅ እየጠፋ ሲሄድ መጨረሻ
ውን እንዳይመለከቱ፣ ፊቱን በጨርቅ እንደ
ሸፈነው እንደ ሙሴ አይደለንም። 14ነገር
ግን ልቡይ ኪዳን በተነበበ ቍጥር ያ መሸ
ፈኛ እስከ ዛሬ ድረስ ስላልተወገደ ልቡና
ቸው እንደ ደነዘዘ ነው፤ መሸፈኛው አሁ
ንም አልተወገደም፤ የሚወገደው በክርስቶስ
ብቻ ነውና። 15እስከ ዛሬም ድረስ የሙሴ
መጻሕፍት በተነበቡ ቍጥር መሸፈኛው ልቡ
ናቸውን ይሸፍናል። 16ነገር ግን አንድ ሰው
ወደ ጌታ ዘወር ሲል መሸፈኛው ይወገ
ዳል። 17ጌታ መንፈስ ነው፤ የጌታም መን
ፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ። 18እኛም
ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር
እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን፣[ሐ] የእርሱን
መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር
እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ
ጌታ ነው።

3፥7 ቍ9:13፤ዘፀ 34፥29-35፤ኢሳ42፥21፤ሮሜ2፥29፤4፥15
3፥9 ቍ7፤ዘዳ27፥26፤ሮሜ1፥17፤3፥21:22
3፥12 ሐሥ4፥29፤ ሮሜ5፥4:5፤8፥24:25
3፥13 ቍ7፤ዘፀ 34፥33
3፥14 ቍ6፤ሐሥ 13፥15፤15፥21፤ሮሜ 11፥7:8፤2ቆሮ4፥4
3፥16 ዘፀ34፥34፤ ኢሳ25፥7፤ሮሜ11፥23
3፥17 ኢሳ61፥1:2፤ ዮሐ8፥32፤ገላ4፥6:7
3፥16 ዘፀ34፥34፤ ኢሳ25፥7፤ሮሜ11፥23
3፥17 ኢሳ61፥1:2፤ ዮሐ8፥32፤ገላ4፥6:7
3፥18 ዮሐ17፥22:24፤ሮሜ8፥29፤1ቆሮ 13፥12፤2ቆሮ4፥4:6
4፥1 ቍ16፤መዝ 18፥45፤ኢሳ40፥31፤ 1ቆሮ7፥25፤1ጢሞ 1፥13:16
4፥2 ሮሜ6፥21፤ 1ቆሮ4፥5፤2ቆሮ2፥17፤ 5፥11፤ዕብ4፥12
4፥3 1ቆሮ1፥18፤ 2ቆሮ2፥12፤3፥14
4፥4 ቍ6፤ዮሐ12፥31

## በሸክላ ውስጥ የተቀመጠ ክቡር ዕቃ

4 ስለዚህ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ
ይህ አገልግሎት ስላለን ተስፋ አንቈር
ጥም። 2ነገር ግን ስውርና አሳፋሪ ነገሮችን
ትተናል፤ አናታልልም፤ የእግዚአብሔርንም ቃል
ከሐሰት ጋር አንቀላቅልም፤ ይልቁንም እው
ነትን በግልጽ እየተናገርን በሰው ሁሉ ኅሊና
ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረን ራሳችንን በእግ
ዚአብሔር ፊት እናቀርባለን።

3ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ፣ የተከ
ደነው ለሚጠፉት ነው። 4የእግዚአብሔር አም
ሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወን
ጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ
የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል።

[ሐ]18 ወይም የጌታን ክብር በጥሞና እያሰላሰልን

ተስፋ ይፈጸም ዘንድ ያንኑ ሕግ፣ "በሰው ልብ ጽላት ላይ" ይጽፈዋል (ቍ3)። በዚህም መሠረት አማኙ ቀደም ሲል ይጠላው የነበረውን የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲወድ ያደርገዋል፤ ሕጉንም ለመጠበቅ ቀድሞ ያልነበረውን ኀይል ይሰጠዋል።

*3፥7-18፤* ጳውሎስ በክርስቶስ ስለ ሆነው የአዲስ ኪዳን፣ "አገልግሎቱ" (ከቍ6፤ 4፥1 ጋር ያነጻጽሩ) ይሟገታል፤ እዚህም ላይ በሲና ተራራ ላይ አሮጌውን ኪዳን ከተቀበለው ከሙሴ አገልግሎት ጋር የራሱን የአዲሱን ኪዳን አገልግሎት ያነጻጽራል። ነገር ግን አሁን፣ "አገልግሎት" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙበት፣ "በድንጋይ ላይ በፊደል የተቀረጸውን" (ቍ7) ሕግና "በሰው ልብ ጽላት ላይ" (ቍ3) የሚጽፈውን መንፈስ ቅዱስን ለመግለጽ ነው። የንጽጽሩ ዐላማ የሙሴ ፊት መንጸባረቅ እየደበዘዘ መሄዱንና የአዲሱ ኪዳን አገልጋዮች ፊት ግን፣ "ከክብር ወደ ክብር እየተለወጠ" መሄዱን ለማሳየት ነው። ይህም የአሮጌውን ኪዳን ጊዜያዊነትና ደካማነት እንዲሁም የአዲሱን ኪዳን ዘላለማዊነትና ብቁነት እንድናይ ይረዳናል።

3፥7 *ከ ... ክብር፤* ሕጉ በተሰጠ ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር አብሮት ስለ ተገለጠ፣ ሙሴ ከተራራው በወረደ ጊዜ ከፊቱ ላይ ይንጸባረቅ ነበር (ዘፀ 34፥29-30 ይመ)። *በክብር ከመጣ፤* በሲና ተራራ ላይ የተሰጠው ሕግ መጥፎ ወይም ክፉ አልነበረም፤ እንዲያውም ጳውሎስ በሌላ ስፍራ ቅዱስ፣ ጻድቅ፣ መልካምና መንፈሳዊ በማለት ይገልጸዋል (ሮሜ 7፥12:14)። ነገር ግን ክፋቱ ያለው ለሕጉ ባለመታዘዝ የሕጉን ፍርድና የሞት ቅጣት በራሳቸው ላይ በሚያመጡ ሰዎች ልብና ተግባር ውስጥ ነው፤ በድንጋይ ጽላት ላይ የተቀረጸውም ሕግ ከእንዲህ ዐይነቱ ክፋት ሊያነጻ አይችልም።

3፥8-9 *የመንፈስ አገልግሎት ... የሚያጸድቀው አገልግሎት፤* በሞት ፈንታ ሕይወትን ይሰጣል። እዚህ ላይ፣ "ጽድቅ" ሲባል እግዚአብሔር እንዲያው የሚሰጠንን ጽድቅ እንዲሁም በእኛ የዕለት ተዕለት ሕይወት ሊታይ የሚገባውን ጽድቅ ያመለክታል።

3፥11 *የሚያልፈው፤* ጳውሎስ እዚህ ላይ በሲና ተራራ ላይ የተሰጠውን አሮጌውንና ለዘላለም የማይኖረውን ኪዳን የሚያልፍ ይለዋል። ይህ የሚያልፈው፣ ጊዜው ሲደርስ በማያልፈውና እጅግ የላቀ ክብር ባለው በአዲሱ ኪዳን ተተክቶአል።

3፥13 *ፊቱን በጨርቅ እንደ ሸፈነ እንደ ሙሴ፤* ዘፀ 34፥33-35 ይመ። የመሸፈኛው ዐላማ የእስራኤል ሕዝብ እየደበዘዘ የሚሄደውን ክብር እንዳያዩ ለማድረግ ነበር።

3፥14 *ያ መሸፈኛ እስከ ዛሬ ድረስ ስላልተወገደ፤* በሙሴ ፊት ላይ የነበረውን የሚጠፋውን ክብር እንዳያዩ ያደረገ መሸፈኛ አሁንም በልባቸው ስላለ፣ ጊዜያዊና ብቃት የሌለውን የአሮጌውን ኪዳን ባሕርይ እንዳያስተውሉ አድርጎአቸዋል፤ ይህ መሸፈኛ ሊወገድ የሚችለው በክርስቶስ ብቻ ነው። አዲሱ ኪዳን ምን ያህል የተሻለ እንደሆነና ከክብሩም ታላቅነት የተነሣ አሮጌውን ኪዳን እንዴት እንደተካው ማወቅ የሚችሉት በክርስቶስ በኩል የተሰጠውን አዲሱን ኪዳን የተቀበሉ ሰዎች ብቻ ናቸው።

3፥17 *ጌታ መንፈስ ነው፤* ይህ አባባል በቍ6 መጨረሻ ላይ፣ "መንፈስ ... ሕይወትን ይሰጣል" ከሚለው ጋር መያያዝ አለበት። ሕጉ በማይታዘዙት ላይ የሚያስከትለው ፍርድና የሞት ቅጣት መሠረዝና ሕይወትን በሚሰጠው በአዲሱ ኪዳን ጸጋ መተካት የሚችለው ወደ ጌታ በመመለስ ብቻ ነው (ቍ16)። በክርስቶስ መንፈስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል እጅግ የቀረበ ግንኙነት ይታያል። ሁለቱም በአማኞች ውስጥ እንደሚኖሩ ተነግሮአል (ሮሜ 8፥9፤ ገላ2፥20)። በሮሜ8፥9-10 ላይ መንፈስ፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የክርስቶስ መንፈስ" እንዲሁም ክርስቶስ አንዱ ሌላውን ተክቶ የገባ ይመስላል። በሐሥ 16፥6-7 ላይ መንፈስ ቅዱስና የኢየሱስ መንፈስ አንድ ይመስላሉ። ይህ የሆነው መንፈስ ቅዱስ የሚሠርጸው ከአብና ከወልድ በመሆኑ ሊሆን ይችላል፤ ደግሞ ሁለቱ የሥላሴ አካላት ዐላማቸውን ከግቡ የሚያደርሱት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው።

3፥18 *ባልተሸፈነ ፊት፤* ሙሴ ካደረገው ጋር ሲነጻጸር ነው። *የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤* ክርስቶስ ራሱ የእግዚአብሔር ክብር ሙሉ በሙሉ መንጸባረቅ ነው (ዕብ 1፥3)፤ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአብ ዘንድ የነበረው ክብሩ የማይሻርና ዘላለማዊ ነው (ዮሐ 17፥5)። በእርሱ የምናምን እኛ ክርስቶስን እየመሰልን በመሄድ የዚሁ ክብር ተካፋዮች እንሆናለን። ይህ የሚያመለክተው የክርስቲያኖችን የቅድስና ሕይወት ሂደት ነው።

4፥1 *ይህ አገልግሎት፤* 3፥6 እና ማብ ይመ። *ተስፋ አንቈርጥም፤* እግዚአብሔር አገልጋዮቹን በምሕረቱ በሚጠራበትና በሚልክበት ጊዜ በመከራና በስደት ውስጥ ጸንተው ማለፍ እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል።

4፥2 *ስውርና አሳፋሪ ነገሮችን ትተናል፤* ጳውሎስ ይህን የሚለው በቆሮንቶስ ስለ ነበሩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ነው። ባንጻሩም ጳውሎስ የገዛ ኅሊናቸውንና በእግዚአብሔር ፊት የነበረውን ቅንነት ምስክር አድርጎ በመቍጠር፣ በፊታቸው ሲመላለስ እውነትን በግልጽ ይናገር እንደነበር ይገልጻል፤ ደግሞም እውነትን ያድበሰበሰበትና ሰዎችን ለማታለል የሞከረበት ጊዜ እንደሌለ ይናገራል (ከ1፥12:18-24 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥3 *ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ፤* 3፥13-18 ይመ።

4፥4 *የእግዚአብሔር አምሳል፤* ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ

5እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ
መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፤ እኛም
ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገል
ጋዮች ሆነናል። 6በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር
የክብሩን ዕውቀት ብርሃን ይሰጠን ዘንድ፣
“በጨለማ ብርሃን ይብራ” ያለው እግዚአ
ብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቶአልና።
7ነገር ግን ይህ እጅግ ታላቅ ኀይል ከእግ
ዚአብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን ለማሳ
የት፣ ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ
አለን። 8ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኰታኰ
ትም፤ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቈርጥም፤
9ብንሰደድም ተጥለን አንቀርም፤ መትተው
ቢጥሉንም አንጠፋም። 10የኢየሱስ ሕይወት
በሰውነታችን እንዲገለጥ፣ የኢየሱስን ሞት
ዘወትር በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን።
11የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋችን
እንዲገለጥ፣ እኛ ሕያዋን የሆንን ሁልጊዜ
ስለ ኢየሱስ ለሞት ዐልፈን እንሰጣለንና።
12እንግዲህ ሞት በእኛ ይሠራል፤ ሕይወት
ግን በእናንተ።
13“አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ” ተብሎ
እንደ ተጻፈ፣ እኛም በዚያው የእምነት
መንፈስ እናምናለን፤ ስለዚህም እንናገራለን፤
14ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስን ከሙታን ያስ
ነሣው እኛንም ደግሞ ከኢየሱስ ጋር አስነ
ሥቶ ከእናንተ ጋር በፊቱ እንደሚያቀርበን
እናውቃለን። 15ለብዙ ሰዎች እየደረሰ ያለው
ጸጋ፣ ለእግዚአብሔር ክብር በምስጋና ላይ ምስ
ጋናን እንዲጨምር ይህ ሁሉ ለእናንተ ጥቅም
ሆኖአል።
16ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤ ውጫዊው
ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣ ውስጣ
ዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፤
17ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከ
ራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር
ያስገኝልናል። 18ስለዚህ ዐይናችን የሚያተ
ኵረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማ
ይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ
ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው።

### ሰማያዊ መኖሪያችን

5 መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን
ቢፈርስም፣ በሰው እጅ ያልተሠራ ነገር
ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰ
ማይ እንዳለን እናውቃለን። 2እስከዚያው

14፥9፤1ቆሮ1፥20፤2ቆሮ3፥14
4፥5 1ቆሮ1፥13፡23፤9፥19
4፥6 ቍ4፤ዘፍ1፥3፤መዝ18፥28፤2ጴጥ1፥19
4፥7 መሳ7፥2፤ኢዮ4፥19፤ኢሳ64፥8፤1ቆሮ2፥5፤2ቆሮ6፥7፤2ጢሞ2፥20
4፥8 2ቆሮ7፥5፤ገላ4፥20
4፥9 መዝ37፥24፤ምሳ24፥16፤ዮሐ15፥20፤ሮሜ8፥35፤ዕብ13፥5
4፥10 ሮሜ6፥5፡6፤2ቆሮ1፥5
4፥11 ሮሜ8፥36
4፥12 2ቆሮ13፥9
4፥13 መዝ116፥10፤1ቆሮ12፥9
4፥14 ሐሥ2፥24፤ኤፌ5፥27፤ቈላ1፥22፤1ተሰ4፥14፤ይሁ24
4፥15 2ቆሮ1፥11
4፥16 ቍ1፤መዝ18፥45፤103፥5፤ኢሳ40፥31፤ሮሜ፥22፤ቈላ3፥10

የእግዚአብሔር ልጅና ሁለተኛው የሥላሴ አካል በመሆኑ፣ እግዚአብሔርን በትክክል ያሳየናል፤ ምክንያቱም እርሱ የመለኮት እውነተኛው መንጸባረቅ ነው (ዕብ 1፥3)። ክርስቶስ የእግዚአብሔር አምሳል ነው፤ ሰውም በመጀመሪያ የተፈጠረው በዚሁ መልክ ሲሆን የተዋጁም ሰዎች ሁሉ ወደዚሁ መልክ በክብር ይለወጣሉ (3፥18)፤ ደግሞም ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፣ እኛ በእርሱ የምናምነው እርሱን ወደ መምሰል እንለወጣለን (1ዮሐ 3፥2)። *የዚህ ዓለም፤* ወደፊት ከሚመጣውና ዘላለማዊ ከሆነው ዓለም ጋር በማነጻጸር ነው፤ በሚመጣው ዓለም የእግዚአብሔር ፍጥረት አሁን ከሚያበላሸውና ከሚያረክሰው ነገር ሁሉ ለዘላለም ይነጻል። በገላ1፥4 ላይ “ክፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም” ተብሎአል። *የዚህ ዓለም አምላክ፤* ትልቁን የእግዚአብሔር ጠላት ዲያብሎስን ነው፤ እርሱ ካለማመንና ከክፋት ሁሉ በስተ ጀርባ ያለ የማይታይ ኀይል ነው። ተከታዮቹም በእርሱ ፈለግ ሲሄዱ አምላካቸው ያደርጉታል። *የማያምኑትን ሰዎች ልቦና አሳውሮአል፤* ወንጌልን የማይቀበሉ ሰዎች መለኮታዊውን ክብር እንዳያዩ የጋረዳቸውን (3፥12-18) መሸፈኛ ምሳሌ በማድረግ ጳውሎስ የጀመረውን ገለጻ ይቀጥላል።

4፥5 *የምንሰብከው ... ራሳችንን አይደለምና፤* ራሳቸውን እንደሚከቡት እንደ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አይደለም። ጳውሎስ በእምነታቸው ላይ ጫና አላደረገም (1፥24)፤ ምክንያቱም ጌታ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ የጳውሎስም ስብከት ዐቢይ ሐሳብ እርሱ ነው።

4፥6 *በጨለማ ብርሃን ይብራ፤* እግዚአብሔር ይህን የተናገረው በፍጥረት መጀመሪያ ነው (ዘፍ 1፥2-4)፤ ደግሞም በአዲስ ፍጥረት ወይም በአዲስ ልደት ጊዜ (5፥17፤ ዮሐ 3፥3፡7፤ 1ጴጥ 1፥3 ይመ)፣ የኀጢአትን ጨለማ በወንጌል ብርሃን ሲያስወግድ ይህንኑ እንደ ገና ተናግሮአል። *የእግዚአብሔርን የክብሩን ዕውቀት ብርሃን፤* በጳውሎስ ልብ የበራው ብርሃን በክርስቶስ ፊት ላይ የታየው የእግዚአብሔር ክብር ዕውቀት ነው፤ ይህም ጳውሎስን ስለ ክርስቶስ ዐዋጅ ነጋሪ ለመሆን አብቅቶታል፤ ክርስቶስም የመጣው ከምድራዊው መገናኛ ድንኳን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በሙሉ ክብሩ ከሚኖርበት ሰማያዊ ስፍራ ነው (ዮሐ1፥14 ይመ)።

4፥7 *ይህ የከበረ ነገር፤* ወንጌልን ነው። *በሸክላ ዕቃ፤* ውድና የከበሩ ነገሮችን ለመሸሸግ ተራ የሆኑና ዐይን የማይገቡ የሸክላ ዕቃዎችን መጠቀም የተለመደ ነበር። እዚህ ላይ የጳውሎስ ሰውነት ደካማና ዐላፊ ጠፊ መሆኑን ለመግለጽ የገባ ነው። *እጅግ ታላቅ ኀይል ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን፤* የሰው ደካማነት የእግዚአብሔርን ብርታት ያሳያል የሚለው ሐሳብ በዚህ መልእክት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል።

4፥10 *የኢየሱስን ሞት ዘወትር በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን፤* እንደ “ሸክላ ዕቃ” በቀላሉ ተሰባሪ የሆነው የጳውሎስ ሰውነት (ቍ7) ለወንጌል ሲል ዘወትር በደረሰበት መከራና ስደት መንገላታቱና በዚህም የክርስቶስ መከራ ተካፋይ መሆኑ (1፥5፤ ሮሜ 8፥17፤ ፊል 3፥10፤ ቈላ 1፥24 ይመ) በግልጽ ታይቶአል።

4፥11 *የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋችን እንዲገለጥ፤* የክርስቶስን የትንሣኤ ሕይወትና ኀይል ያመለክታል። የሰው ደካማነት የእግዚአብሔርን ብርታት እንደሚያሳይ እንደገና (የቍ7 ማብ ይመ) እዚህ ላይ ተነግሮአል፤ በየዕለቱ፣ “መሞትም” በየዕለቱ የሚገኘውን ድንቅ የትንሣኤ ሕይወት አጕልቶ ያሳያል (1፥9 ይመ)።

4፥13 *አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ፤* መዝ 116፥10 ይመ። ያመነ ሰው ይመሰክራል። ጳውሎስም የወንጌልን መልእክት ለሌሎች ለማድረስ ሳይታክት ከቦታ ወደ ቦታ የተዘዋወረውና የደከመው ለዚሁ ነው።

4፥16 *ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤* የቍ1 አባባል እዚህ ላይ ተደግሞአል፤ በመኻል ጣልቃ የገቡት አንቀጾች፣ ሐዋርያው ለምን ልበ ሙሉ እንደ ሆነ የሚያስረዱ ሲሆን፣ ቀሪው የምዕራፉ ቍጥሮችም ከላይ በዝርዝር ያወሳውን ጭብጥ የሚያጠቃልሉ ናቸው። *እየጠፋ ቢሄድም፤* ከደረሰበት መከራ የተነሣ ነው። *ይታደሳል፤* በውስጡ ከሚነደውና ከማይጠፋው የኢየሱስ የትንሣኤ ሕይወት የተነሣ ነው፤ ደግሞም የውስጡ ሰውነት መታደስ ከውጭ የሚመጣውን መከራ ያሸንፋል፤ የኋላ ኋላም ሞትን ድል ይነሣል።

4፥17 *ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን፤* በክርስቲያኖች ላይ ምንም ዐይነት መከራ ቢደርስ፣ ሊመጣ ካለው ዘላለማዊ ሕይወት አንጻር ሲታይ ስፍራ የሚሰጠው አይደለም። *ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር፤* ዘላለማዊው ክብር በዚህ ምድር ከሚደርስብን መከራ ጋር ሲነጻጸር እጅግ ታላቅ ክብር ነው (ከሮሜ 8፥18 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥18 *የሚታየው ... የማይታየው፤* ክርስቲያኖች በገሃዱ ዓለም ሲኖሩ የሚያዩትና የሚያሳልፉት ሕይወት አብዛኛውን ጊዜ የሚያስጨንቅና ግራ የሚያጋባ ነው፤ ይሁን እንጂ በወደቀውና ዐላፊ ጠፊ በሆነው ዓለም የሚደርስባቸው መከራ ሁሉ ጊዜያዊ ነው። ዐይናችንን በዚህ በሚታየው ነገር ላይ ማሳረፍ ተስፋ እንድንቈርጥ ያደርገናል (ቍ1፡16)። ባንጻሩም የማይታየው ዓለም ዘላለማዊና የማይጠፋ ነው፤ የማይታየው ዓለም የማይታይ በመሆኑ የለም ማለት አይደለም (ከዕብ11፥1፡6፡26-27 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህም የተነሣ ዐይናችንን፣ ጸንቶ ከማይኖረው ከዚህ ዓለም መልክ ላይ አንሥተን ጸንቶ ወደሚኖረው ወደ ላይኛው ዓለም እንመለከታለን (ፊል3፥20፤ ዕብ12፥2 ይመ)።

5፥1 *መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን፤* አሁን ያለውን ሥጋዊ አካላችንን ነው (2ጴጥ1፥13 ይመ)። ድንኳን ጊዜያዊና ተራ መኖሪያ እንደ ሆነ ሁሉ ሥጋዊ አካላችንም ደካማ፣ ለጕዳት የተጋለጠና ፈራሽ ነው (4፥10-12፡16)። *ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰማይ፤* ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊና ጽኑ ቤት ነው። ይህም አሁን ከማይታዩት እውነታዎች አንዱ ነው (4፥18)። *በሰው እጅ ያልተሠራ፤* የእግዚአብሔር ሥራ ስለ ሆነ

ግን የሰማዩን መኖሪያችንን ለመልበስ እየና
ፈቅን እንቃትታለን፤ 3በእርግጥ ከለበስነው ራቍ
ታችንን ሆነን አንገኝም። 4በዚህ ድንኳን
እስካለን ድረስ ከብዶን እንቃትታለን፤ ምክ
ንያቱም ሟች የሆነው በሕይወት እንዲዋጥ
ሰማያዊውን መኖሪያችንን ልንለብስ እንጂ
ልንገፈፍ አንፈልግም። 5ለዚህ ዐላማ ያዘጋ
ጀን እግዚአብሔር ነው፤ ሊመጣ ላለው ዋስ
ትና እንዲሆነን መንፈሱን መያዣ አድርጎ
የሰጠንም እርሱ ነው።

6ስለዚህ ሁልጊዜ በመታመን እንኖራለን፤
በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደ
ምንገኝ እናውቃለን፤ 7ምክንያቱም የምን
ኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም።
8ከሥጋ ተለይተን ከጌታ ጋር መኖርን እን
ደምንመርጥ እርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ።
9ስለዚህ በሥጋ ብንኖርም ወይም ከሥጋ
ብንለይም ዐላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት
ነው። 10ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወን
በር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው
በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ
ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል።

4፥17 መዝ30፥5፤ ሮሜ8፥18፤1ጴጥ1፥6፡7
4፥18 ሮሜ8፥24፤ 2ቆሮ5፥7፤ ዕብ11፥1
5፥1 ኢሳ38፥12፤ 1ቆሮ15፥47፤2ጴጥ1፥13፡14
5፥2 ቍ4፤ሮሜ8፥23፤1ቆሮ15፥53፡54
5፥4 ቍ2፤ሮሜ8፥23 1ቆሮ15፥53፡54
5፥5ሮሜ8፥23፤2ቆሮ1፥22፤ኤፌ1፥13፡14
5፥7 1ቆሮ13፥12፤ 2ቆሮ4፥18
5፥8 ዮሐ12፥26
5፥9 ሮሜ14፥18፤ ኤፌ5፥10፤ቈላ1፥10፤ 1ተሰ4፥1
5፥10 ማቴ16፥27፤ ሐሥ10፥42፤ሮሜ 2፥16፤14፥10፤ኤፌ 6፥8
5፥11 ኢዮ23፥15፤ 2ቆሮ4፥2፤ዕብ10፥31፤ 12፥29፤ ይሁ23
5፥12 2ቆሮ1፥14፤ 3፥1
5፥13 2ቆሮ11፥1፡6፡17፤12፥11

## የማስታረቅ አገልግሎት

11እንግዲህ ጌታን መፍራት ምን ማለት
እንደ ሆነ ስለምናውቅ፣ ሰዎች የምንናገረ
ውን እንዲቀበሉ ለማድረግ እንጥራለን።
የእኛ ማንነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ
ነው፤ ደግሞም በኅሊናችሁ ዘንድ ግልጽ ነው
ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። 12ይህን የምለው
ራሳችንን በእናንተ ፊት እንደገና ለማመስ
ገን ሳይሆን፣ በእኛ እንድትመኩ ዕድል ልሰ
ጣችሁ ነው፤ ይኸውም በውጭ በሚታየው
ለሚመኩት እንጂ በልብ ውስጥ ባለው
ነገር ለማይመኩ መልስ መስጠት እንድት
ችሉ ነው። 13ከአእምሮ ውጪ ብንሆን ስለእግዚ
አብሔር ብለን ነው፤ ባለ አእምሮም ብንሆን
ለእናንተ ነው። 14የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለ
ናልና፤ ምክንያቱም አንዱ ስለ ሁሉ እንደ
ሞተ እርግጠኞች ሆነናል፣ ከዚህም የተነሣ
ሁሉ ሞተዋል። 15በሕይወት ያሉትም ለሞ
ተላቸውና ከሙታን ለተነሣላቸው እንጂ
ከእንግዲህ ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለ
ሁሉ ሞተ።

5፥14 ሮሜ6፥6፡7፤ገላ2፥20፤ቈላ3፥3 5፥15 ሮሜ4፥25፤ 14፥7-9

ፍጹምና ዘላለማዊ ነው (ዕብ 9፥11 ይመ)።

5፥2 *እስከዚያው ግን፤* የጌታን ዳግም ምጽአት ስንጠባበቅ ነው። *እንቃትታለን፤* የምንቃትተው ክቡር የሆነውን መንፈሳዊ አካል ለብሰን ፍጹማን ለመሆን ስለምንናፍቅ ነው (ከ1ቆሮ 15፥42-49 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሰማዩን መኖሪያችንን ለመልበስ፤* እግዚአብሔር የሚሰጠን ዘላለማዊ መኖሪያ በሚለበስ ልብስ ተመስሎአል።

5፥3 *ራቍታችንን፤* እንደ ድንኳን የሆነው ምድራዊ መኖሪያቸው በሞት እንደፈረሰባቸው ሰዎችና ያለ አካል እንደ ቀሩት ማለት ነው (የቍ8 ማብ ይመ)።

5፥4 *ሟች የሆነው፤* የአሁኑን ሟች አካላችንን ያመለክታል። *በሕይወት እንዲዋጥ፤* በኢየሱስ የትንሣኤ ሕይወት ተካፋይ ስለ ሆንን (4፥10)፣ ሟች የሆነው ሰውነታችን የሚዋጠው በሞት ሳይሆን በሕይወት ነው። ሞትና መቃብር ዋጭ ስልቃጭ መሆናቸው ለብዙ ዘመን ሲነገር ኖሮአል (መዝ 69፥15፤ ምሳ 1፥12 ይመ)፤ እንደ ኢሳይያስ ሁሉ (ኢሳ 25፥8 ይመ፤ በተጨማሪ 1ቆሮ 15፥54 ይመ) ጳውሎስም ሞት እንደሚዋጥ ይናገራል።

5፥5 *እግዚአብሔር ... መንፈሱን ... የሰጠንም፤* ከሞት በተነሣውና በከበረው አዳኝ አማካይነት የፈሰሰው መንፈስ ቅዱስ፣ በክርስቶስ የመቤዠት ሥራ የሚገኘውን በረከት በአማኞች ልብ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፤ የኢየሱስንም የትንሣኤ ኀይል በየዕለቱ እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል (ከ4፥14፡16 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህም አማኞች የኋላ ኋላ የከበረውን የክርስቶስን አካል ለመምሰል እየተለወጡ እንደሚሄዱ ያረጋግጣል (ፊል 3፥21)። *መያዣ፤* የ 1፥22 ማብ ይመ።

5፥6 *በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደምንገኝ፤* መኖሪያችን በሆነው ምድራዊ ድንኳን እስካለን ድረስ ማለት ነው (ቍ1)፤ ይህም ማለት በዚህ ምድር ስንኖር ጌታ በመንፈሱ ከእኛ ጋር የለም ማለት አይደለም።

5፥8 *ከሥጋ ተለይተን ከጌታ ጋር መኖርን፤* ክርስቲያኖች በሞት "ከምድራዊ ድንኳናቸው" ከተለዩ በኋላ (ቍ1) ያሉብትን ሁኔታ ያሳያል። ይህም ሁኔታ በሞትና በትንሣኤ መካከል ምናልባትም ከምድራዊ ድንኳናችን ተለይተን ሰማያዊ አካላችንን ገና ሳንለብስ ያለውን ጊዜ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ መኖራችንንም ሆነ ማንነታችንን አንስትም፤ ምክንያቱም በአካለ ሥጋ የሌለ አማኝ የሚኖረው ከጌታው ጋር ነው፤ እንዲያውም ከጌታ ጋር መኖር በአካለ ሥጋ ከመኖር ይሻለዋል (ከፊል1፥23 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥9 *በሥጋ ብንኖርም ወይም ከሥጋ ብንለይም፤* ጌታ በሚመጣበት ጊዜ በሕይወት ብንሆንም ወይም ሞተን ሳለን ቢመጣም ማለት ነው።

5፥10 *በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤* ክርስቲያኖች በእምነት አማካይነት በክርስቶስ ያገኙትን ዘላለማዊ ጽድቅ የሚመለከት ሳይሆን፣ በዚህ ምድር ሲኖሩ ለሠሩት ሥራ የሚቀበሉት ፍርድ ነው (ከ1ቆሮ 3፥11-15 ጋር ያነጻጽሩ)። *በሥጋው ለሠራው ... ሥራ፤* ምንም እንኳ ሥጋ ዐላፊ ጠፊ ቢሆንም በሥጋ ሳለን ላደረግነው ነገር ሁሉ ተጠያቂ ነን። ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችም በሠሩት ሥራ ሁሉ ለፍርድ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባሉ (ሮሜ 2፥5፡16 ይመ)፤ እዚህ ላይ ግን ጳውሎስ የሚናገረው ስለ አማኞች ነው።

5፥11 *ጌታን መፍራት፤* አንድ ቀን በፊቱ ቀርበን እንደ ምንጠየቅ በማሰብ ነው (ቍ10)። *ሰዎች የምንናገረውን እንዲቀበሉ ለማድረግ እንጥራለን፤* ጳውሎስ በመካከላቸው ሠርገው የገቡት ሐሰተኞች አስተማሪዎች ሳይሆኑ፣ እርሱ ብቻ እውነተኛ ሐዋርያ እንደ ሆነ አንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በሚገባ ማሳመን ነበረበት።

5፥12 *በውጭ በሚታየው ለሚመኩት፤* የሐሰት ሐዋርያት ሽርጉድ ለይስሙላ ነበር፤ ዐላማቸውም እውነተኛና ጥልቅ መንፈሳዊ ነገር ሳይሆን፣ ገንዘብና ዝና እንዲሁም የግል ክብር ነበር።

5፥13 *ከአእምሮ ውጪ ብንሆን ... ባለ አእምሮም ብንሆን፤* ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ አገኘሁ የሚለውን አስገራሚ የሕይወት ለውጥ ተቃዋሚዎቹ እንደ እብደት ቈጥረውበት፣ በሃይማኖት ነገር አእምሮውን ስቶአል ሳይሉት አልቀሩም። ይህ አእምሮውን እንደሳተ ሰው የሚያስቈጥረው ከሆነ፣ ጳውሎስ ነገሩን ሲክድ አናይም፤ ምክንያቱም መልእክቱ ሙሉውን እንደሚያወሳው ጳውሎስ ለወንጌል ሲል መከራን በፈቃደኝነትና በደስታ ተቀብሎአል (ከ12፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። በመሠረቱ ይህ በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ጒዳይ ነው። በሌላም በኩል ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ወንጌልን ሲሰብክ እንደ እብድ የሚያስቈጥረው ምንም ነገር አልነበረም፤ ምክንያቱም ወንጌልን በሰበከበት ጊዜ ሁሉ እስከ መጨረሻው የረጋና የሰከነ ሰው ነበር፤ ደግሞም ባነጋገሩ ምንም ዐይነት ስሜታዊነትና አፈ ጮሌነት አልታየበትም (ከ1ቆሮ 2፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥14 *የክርስቶስ ፍቅር፤* በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ፍቅር፣ "እኛ ለክርስቶስ ያለንን ፍቅር" ነው የሚሉ ሰዎች ቢኖሩም፣ የሚያሳየው ግን ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞት የተገለጸውን ፍቅር ነው። *አንዱ፤* በሥጋ የተገለጠውን ወልድ ነው። *ስለ ሁሉ፤* ለሰው ልጆች ሁሉ ነው። *ከዚህ የተነሣ ሁሉ ሞተዋል፤* ክርስቶስ ስለ ሁሉ በመሞቱ፣ ሁሉ በሞቱ እንዲካፈሉ አደረገ። ለአንዳንዶች ሞቱ የራሳቸውን ሞት ያረጋግጥባቸዋል፤ ነገር ግን በእምነት ከክርስቶስ ጋር ለተባበሩት ሞቱ ለኀጢአትና ለእኔነት መሞታቸውን ይገልጻል፤ ስለዚህ አሁን የሚኖሩት ከሙታን ከተነሣው ክርስቶስ ጋር ነው (ቍ15)። ይሁን እንጂ ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ስለ ክርስቶስ የማስተስረይ ሥራ ሳይሆን የክርስቶስ ሞት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ስለሚያስገኘው ውጤት ነው የሚሉ አሉ። ስለዚህ፣ "ሁሉም" የሚለው ቃል

[16]ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በውጫዊ
ነገር አንመዝንም፤ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን
በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፤ ከእንግዲህ
ግን እንደዚህ አናደርግም። [17]ስለዚህ ማንም
በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮ
ጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል።
[18]ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እርሱ በክርስ
ቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፤ የማ
ስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፤ [19]እግዚአብሔር
በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ
የሰዎችን በደል አይቈጥርባቸውም ነበር፤
ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን።
[20]ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤
እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀ
ርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ
ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን። [21]እኛ
በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድን
ሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአ
ብሔር ስለ እኛ ኀጢአት[*] አደረገው።

6 ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ እንደ
መሆናችን መጠን፣ የተቀበላችሁትን የእግ
ዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉት ዐደራ
እንላችኋለን። [2]እርሱ፣

"በትክክለኛው ሰዓት ሰማሁህ፤
በመዳንም ቀን ረዳሁህ" ይላልና።
እነሆ፤ ትክክለኛው ሰዓት አሁን ነው፤
የመዳንም ቀን አሁን ነው።

## ጳውሎስ የተቀበለው መከራ

[3]አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ፣ ለማንም
ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም። [4]ይሁን እንጂ
በምናደርገው ነገር ሁሉ ራሳችንን እንደ
እግዚአብሔር አገልጋዮች እናቀርባለን፡- በብዙ
ትዕግሥት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣
[5]በመገረፍ፣ በመታሰር፣ በሁከት፣ በሥራ
ብዛት፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመራብ፣ [6]በን
ጽሕና፣ በዕውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣
በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር፣ [7]በእ
ውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኀይል፣ በቀኝና
በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመያዝ፣
[8]በክብርና በውርደት፣ በመመስገንና በመሰ
ደብ፣ ኖረናል፤ ደግሞም እውነተኞች ስን
ሆን ሐሰተኞች ተብለናል፤ [9]የታወቅን ስን
ሆን እንዳልታወቅን ሆነናል፤ ሞተዋል ስን
ባል እነሆ በሕይወት አለን፤ ብንደበደብም
አልተገደልንም፤ [10]ሐዘንተኞች ስንሆን ሁል
ጊዜ ደስተኞች ነን፤ ድኾች ስንሆን ብዙዎ
ችን ባለጠጎች እናደርጋለን፤ ምንም የሌለን
ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።

[11]የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፤ ሁሉን በግልጽ ነግ
ረናችኋል፤ ልባችንንም ወለል አድርገን ከፍ
ተንላችኋል። [12]ፍቅራችሁን የነፈጋችሁን እና
ንተ ናችሁ እንጂ እኛስ ፍቅራችንን አልነፈ
ግናችሁም። [13]ልጆቼ እንደ መሆናችሁ መጠን
ይህን አሳስባችኋለሁ፤ እናንተም በዚያው
ልክ ልባችሁን ወለል አድርጋችሁ ክፈቱልን።

## ከማያምኑ ሰዎች ጋር አለመተባበር

[14]ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ
መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፅ ጋር

[*]21 ወይም የኀጢአት መሥዋዕት

5፥16 2ቆሮ10፥4፤
11፥18
5፥17 ኢሳ65፥17፤
ዮሐ1፥13፤ሮሜ6፥4
፤16፥3፤ገላ6፥15፤ራእ
21፥4:5
5፥18 ሮሜ5፥10፤
11፥36
5፥19 ሮሜ4፥8
5፥20 ቈላ1፥8፤ኢሳ
27፥5፤2ቆሮ6፥1፤ኤፌ
6፥20
5፥21 ሮሜ1፥17፤
1ቆሮ1፥30፤ዕብ4፥15
፤7፥26፤1ጴጥ2፥22:24
፤1ዮሐ3፥5
6፥1 1ቆሮ3፥9፤
15፥2፤2ቆሮ5፥20
6፥2 መዝ69፥13፤
ኢሳ49፥8፤55፥6
6፥3 ማቴ5፥29፤ሮሜ
14፥13:20፤1ቆሮ8፥9:
13፤9፥12፤10፥32
6፥5 ሐሥ16፥23፤
1ቆሮ4፥11፤2ቆሮ11፥
23-25
6፥6 ሮሜ12፥9፤
1ቆሮ 2፥4፤1ተሰ1፥5
፤1ጢሞ1፥5
6፥7 ሮሜ13፥12፤
2ቆሮ4፥2:7፤10፥4፤
ኤፌ6፥10-18
6፥8 ማቴ27፥63
፤1ቆሮ4፥10:13
6፥9 ሮሜ8፥36፤
2ቆሮ1፥8-10፤4፥10
:11
6፥10 ማቴ5፥12፤
ሐሥ3፥6፤ሮሜ8፥32
፤1ቆሮ3፥21፤2ቆሮ7፥4
፤8፥9፤ፊል2፥17፤4፥4
፤ቈላ1፥24፤1ተሰ1፥6

ባጠቃላይ የሰው ልጆችን ሁሉ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ያመለክታል ይላሉ።

5፥16 *ከዚህ ቀደም ክርስቶስን በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፤* ጳውሎስ በክርስቶስ ከማመኑ በፊት፣ ስለ ክርስቶስ የነበረው አመለካከት በሥጋዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ እንደ ነበር ይገልጻል።

5፥17 *በክርስቶስ፤* በእምነት አማካይነት ከክርስቶስ ጋር መተባበርና ራስን ለእርሱ መስጠት ነው። *አዲስ ፍጥረት፤* መቤዠት ሲባል እግዚአብሔር በፍጥረቱ የነበረው ዐላማ ወደ ቀድሞው ስፍራ መመለሱንና ከፍጻሜ መድረሱን ያሳያል (የ4፥6 ማብ ይመ)፤ ይህም የሚሆነው ሁሉም ነገር በእርሱ በሆነውና (ዮሐ 1፥3፤ ቈላ 1፥16፤ ዕብ 1፥2 ይመ) ሁሉም ነገር በእርሱ አዲስ በሆነው (ከሮሜ 8፥18-23፤ ከኤፌ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ) በክርስቶስ አማካይነት ነው።

5፥18 *ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤* የመቤዠት ሥራ ምንጩ እግዚአብሔር ነው (ሮሜ 5፥8፤ ዮሐ 3፥16 ይመ)፤ ደግሞም የሚያጸናውና ከፍጻሜ የሚያደርሰው እርሱ ራሱ ነው። *የማስታረቅንም አገልግሎት፤* እኛ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅን ሰዎች፣ እንደ ጳውሎስ የእግዚአብሔር መሣሪያዎች በመሆን የዕርቁን መልእክት በዓለም ዙሪያ ሁሉ (ቍ 19) የማወጅ ዕድል ተሰጥቶናል፤ ኀላፊነትም ተቀብለናል።

5፥21 *ኀጢአት የሌለበትን ... ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው፤* የወንጌልን አስፈላጊነትና መልእክት ባጭሩ የሚያቀርብ ነው። ፍጹም ጻድቅ የሆነው ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ በደላችንን ተሸከመ፤ ለእኛም የሚገባውን የሞትና ከእግዚአብሔር የመለየት ቅጣት ተቀበለ። ስለዚህ በድንቅ አሠራሩ እርሱ በእኛ ቦታ በመተካት፣ ጽድቁን ለመጐናጸፍና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ አስቻለን። በእግዚአሔር ፊት ልንቆምና ተቀባይነትም ልናገኝ የቻልነው በእርሱ ብቻ ነው (ከ1ቆሮ 1፥30 ጋር ያነጻጽሩ)። ደግሞም ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፤ ሁሉንም በነጻ ልናገኝ የቻልነው ከመለኮታዊው ጸጋ የተነሣ ነው።

6፥1 *የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉት፤* ጸጋውን ከንቱ ከምናደርግበት መንገድ አንዱ ለራስ ብቻ መኖር ነው (5፥15 ይመ)።

6፥2 *ትክክለኛው ሰዓት ... የመዳንም ቀን፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ የማዳን ሥራውን ሲሠራ በጥቅሉ የሚሆነውን የሚገልጽ ቢሆንም፣ ይበልጡኑ ይህ እውን ሲሆን የምናገኘው በዚህ በጸጋው ዘመን ማለትም በሁለቱ የክርስቶስ ምጽአቶች (በመወለዱና በዳግም መምጣቱ) መካከል ነው። እንዲህ ሲባል ግን ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩት ሕዝቦቹ ከጸጋውና ከማዳኑ ውጭ ናቸው ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን አማኞች በክርስቶስ የተፈጸመውን ተስፋ አስቀድመው ተቀብለዋል (1፥20)፤ ደግሞም ተስፋው ሲፈጸም ከሩቅ በማየት ገንዘባቸው አድርገውታል (ዮሐ8፥56፤ ዕብ11፥13 ይመ)።

6፥3 *ለማንም ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም፤* ጳውሎስ አገልግሎቱ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር አርአያነት ያለው ሕይወት ለመኖር ይጥራል።

*6፥4-10፤* ከ4፥8-12 ጋር ያነጻጽሩ።

6፥4 *ራሳችንን እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች እናቀርባለን፤* በቆሮንቶስ የሰበከው ወንጌል አደጋ ላይ ስለ ነበር፣ ጳውሎስ እንደ ገና ስለ ማንነቱ መናገር ነበረበት፤ ይሁን እንጂ ይህን የሚያደርገው ለራሳቸው ጥቅም እንደሚሯሯጡት ሐሰተኞች ሐዋርያት ሳይሆን፣ እንደ እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው።

6፥10 *ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን፤* በክርስቶስ ነው። እውነተኛ ሀብት ምድራዊ ብልጽግና ሳይሆን፣ "በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ" መሆን ነው (ሉቃ 12፥15:21)። አማኞች የዚህ ዓለም ሀብት ባይኖራቸውም የሁሉ ባለቤት በሆነው ጌታ ሁሉ ነገር አላቸው (ከ1ቆሮ 1፥4-5፤ 3፥21-23፤ ኤፌ 2፥7፤ 3፥8፤ ፊል 4፥19፤ ቈላ 2፥3 ጋር ያነጻጽሩ)።

*6፥11-13፤* ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጋር የነበረው ግንኙነት በግልጽነትና በቅንነት ላይ የተመሠረተ ነበር (ከ1፥12-14፤ 4፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በመካከላቸው የነበሩት ሐሰተኞች ሐዋርያት ግን ጳውሎስ በእርግጥ እንደማይወዳቸው ለማሳመን ይጥሩ ነበር። ስለ ዚህ ሐዋርያው ከልብ እንደሚወዳቸው በትሕትና ይገልጽላቸዋል።

6፥14 *ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ መንገድ አትጠመዱ፤* ጳውሎስ ይህን ሲናገር በዘዳ 22፥10 ላይ እንዱን

ምን ግንኙነት አለው? ብርሃንስ ከጨለማ
ጋር ምን ኅብረት አለው? 15ክርስቶስ ከቤል
ሆር‶ ጋር ምን ስምምነት አለው? የሚያ
ምን ከማያምን ጋር ምን ኅብረት አለው?
16የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር
ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የሕያው እግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ነን፤ እግዚአብሔርም እን
ዲህ ሲል ተናግሮአል፤ "ከእነርሱ ጋር እኖ
ራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አም
ላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።"

17"ስለዚህ ከመካከላቸው ውጡ፤
ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤
ይላል ጌታ።
ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ፤
እኔም እቀበላችኋለሁ።"
18"እኔ አባት እሆናችኋለሁ፤
እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ
ትሆናላችሁ፤
ይላል ሁሉን የሚችል ጌታ።"

7 እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ
ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያ
ረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔ
ርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድ
ርገው።

**የጳውሎስ ደስታ**

2ልባችሁን አስፋልን፤ እኛ ማንንም አልበ
ደልንም፤ ማንንም ወደ ብልሹነት አልመራ
ንም፤ ማንንም አላታለልንም። 3ይህን የም
ለው ልኰንናችሁ አይደለም፤ ምክንያቱም
ከዚህ በፊት እንደ ነገርኋችሁ፣ በልባችን
ውስጥ ስፍራ አላችሁ፤ ስለዚህ ብንኖርም
ብንሞትም አብረን ነው። 4በእናንተ ላይ

6፥11 2ቆሮ7፥3
6፥13 2ቆሮ7፥2፤ 1ተሰ 2፥11
6፥14 ዘፍ24፥3፤ዘዳ 22፥10፤1ቆሮ5፥9፡10፤ 6፥6፤ኤፌ5፥7፡11፤ 1ዮሐ1፥6
6፥15 ሐሥ5፥14፤ 1ቆሮ6፥6፤10፥21፤
6፥16 ዘሌ26፥12፤ ኤር32፥38፤ሕዝ37፥ 27፤ማቴ16፥16፤1ቆሮ 3፥16፤10፥21፤ራእ 21፥3
6፥17 ኢሳ52፥11፤ ሕዝ20፥34፡41፤ራእ 18፥4
6፥18 ዘፀ4፥22፤ 2ሳሙ 7፥18፡4፤ዜና 17፥13፤ኢሳ43፥6፤ ሮሜ 8፥14
7፥1 1ቆሮ10፥14 ፤2ቆሮ6፥17፡18፤1ተሰ 4፥7፤1ጴጥ1፥15፡16
7፥2 2ቆሮ6፥12፡13
7፥3 2ቆሮ6፥11፡12 ፤ፊል1፥7
7፥4 ቍ13፡14፤2ቆሮ 6፥10፤8፥24
7፥5 ዘዳ32፥25፤ ሐሥ16፥9፤2ቆሮ 2፥13፤4፥8
7፥6 ቍ13፤2ቆሮ 1፥3፡4፤2፥13
7፥8 2ቆሮ2፥2፡4
7፥10 ሐሥ11፥18
7፥11 ቍ7
7፥12 ቍ8፤1ቆሮ 5፥1፡2፤2ቆሮ2፥3፡9
7፥13 ቍ6፤2ቆሮ 2፥13
7፥14 ቍ4፡6
7፥15 መዝ55፥5፤ 1ቆሮ 2፥3፤2ቆሮ2፥9 ፤10፥6፤ፊል2፥12

ያለኝ እምነት ትልቅ ነው፤ በእናንተም ላይ
ያለኝ ትምክሕት ትልቅ ነው፤ እንዲሁም
እጅግ ተጽናንቻለሁ፤ በመከራችንም ሁሉ
ደስታዬ ወሰን የለውም።
5ወደ መቄዶንያ በመጣን ጊዜ ከየአቅጣ
ጫው መከራ ደረሰብን እንጂ ሰውነታችን ዕረ
ፍት አላገኘም፤ ከውጭ ጠብ፣ ከውስጥ ደግሞ
ፍርሀት ነበረብን። 6ይሁን እንጂ ሐዘንተኞ
ችን የሚያጽናና እግዚአብሔር በቲቶ መምጣት
አጽናናን። 7የተጽናናነውም በመምጣቱ ብቻ
ሳይሆን፣ እርሱንም ልታጽናኑት በመቻላችሁ
ጭምር ነው። ስለ ናፍቆታችሁ፣ ስለ ሐዘና
ችሁና ለእኔም ስላላችሁ ቅናት ነግሮናል፤
ስለዚህ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ደስ ብሎ
ኛል።
8በመልእክቴ ባሳዝናችሁም በዚህ አል
ጸጸትም፤ ብጸጸትም እንኳ መልእክቴ ያሳዘ
ናችሁ ለጥቂት ጊዜ እንደ ሆነ ተረድቻ
ለሁ። 9አሁን ግን ደስ ብሎኛል፤ ደስታዬም
ስላዘናችሁ ሳይሆን፣ ሐዘናችሁ ንስሐ ለማግ
ባት ስላበቃችሁ ነው፤ ምክንያቱም ሐዘና
ችሁ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ ከእኛ
የተነሣ ምንም አልተጐዳችሁም። 10እንደ
እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ወደ ድነት
ለሚያደርስ ንስሐ ያበቃል፤ ጸጸትም የለበ
ትም። ዓለማዊ ሐዘን ግን ለሞት ያበቃል።
11ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው
ሐዘን እንዴት ያለ ትጋት፣ እንዴት ያለ መልስ
የመስጠት ችሎታ፣ እንዴት ያለ ቍጣ፣
እንዴት ያለ ፍርሀት፣ እንዴት ያለ ናፍ
ቆት፣ እንዴት ያለ በጎ ቅናት፣ እንዴት ያለ
ተግሣጽ እንዳስገኘላችሁ ተመልከቱ። በዚ
ህም ጕዳይ ንጹሓን መሆናችሁን በሁሉ

‶15 ግሪኩ *ቤሊየር* ይላል

---

ከሌላው፣ "አትቀላቀሉ" የሚለውን ትእዛዝ እያሰበ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ምንም እንኳ የቆሮንቶስ አማኞች በሚያባብሉና በሚያታልሉ (የ11፥13-14 ማብ ይመ) ሐሰተኞች መምህራን ቢከበቡም፣ ከእነዚህ የሰይጣን አገልጋዮች ጋር ተባበሩ ማለት ያለ አቻ ተጠመዱ ማለት ነው፤ ይህም በክርስቶስ አንድ ያደረጋቸውን ኅብረትና አንድነት የሚያደፈርስ ነው።

6፥15 *ቤልሆር!* ለሰይጣን የተሰጠ የዕብራይስጥ መጠሪያ ነው (የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ)።

6፥16 *የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው?* ስለ ወንጌል ሲሉ ጥለው ወደ መጡት የጣዖት አምልኮ መመለስ ወይም ከዚያ ጋር ተስማምቶ መኖር የማይገባ ነው (ከ1ተሰ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ!* ይህ ቤተ መቅደስ የሚሠራው፣ "በሕያዋን ድንጋዮች" ማለትም በክርስቲያን አማኞች (1ጴጥ 2፥5) ነው፤ ስለዚህ ከርኵሰትና ቅድስና ከጐደለው ነገር ሁሉ መለየት አለበት (ከ1ቆሮ 6፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥1 *ቅድስናችንን!* 1ተሰ 4፥7፤ 1ዮሐ 3፥3 ይመ።

7፥2 *ማንንም አላታለልንም!* ሐሰተኞች መምህራን እነርሱ ራሳቸው የሚፈጽሙትን ተግባር በጳውሎስ ላይ በመላከክ በክፋት፣ በአጥፊነትና በአጭበርባሪነት ሲወነጅሉት እንደ ነበር ያመለክታል።

*7፥3!* ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያለውን ጥልቅ ፍቅር እንደገና ይገልጻል፤ እነርሱም በበኩላቸው ሐሰተኞች መምህራን የሚነግሯቸውን ትተው ትክክለኛ ሐዋርያቸው እንደ መሆኑ መጠን ፍቅሩን እንዲገልጹለት ያሳስባል (ከ6፥11-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥4 *እምነት ትልቅ ነው ... ደስታዬ ወሰን የለውም!* በ2፥14 ላይ ከዋናው ሐሳብ በመውጣት የጀመረውን ረጅም ገለጻ በዚህ የደስታ መግለጫ ያጠቃልላል። ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ይጠብቅ የነበረው ዜና መልካም ሆኖ ስላገኘው ከመጠን በላይ ተደስቶአል።

7፥5-6 *ወደ መቄዶንያ በመጣን ጊዜ ... አምላክ በቲቶ መምጣት አጽናናን!* ጳውሎስ በ2፥12-13 ላይ ጀምሮት የነበረውን ትረካ እዚህ ላይ ይቀጥላል፤ በዚያ ክፍል ቲቶን በጢሮአዳ ለማግኘት ተስፋ አድርጎ እንዳልተሳካለትና ጕዞውን ወደ መቄዶንያ እንደቀጠለ ገልጾአል። በዚህ ክፍል ደግሞ መቄዶንያ እንደ ደረሰ በቲቶ መምጣት መጽናናቱን ይናገራል፤ የቆሮንቶስ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመስማት እጅግ ጓጉቶ ሳለ ዜናውን ያመጣለት እርሱ ነበርና። ቲቶ ራሱ በቆሮንቶስ የተደረገለት አቀባበል መልካም ነበር፤ ስለዚህ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለጳውሎስ ስለ ነበራቸው፣ "ናፍቆት በጎ ቅናት" (ቍ7 ይመ) እንዲሁም በጳውሎስ ላይ ስላደረሱት የልብ መሰበር የተሰማቸውን፣ "ሐዘን" ሊያረጋግጥለት ችሎአል፤ በመሆኑም፣ "ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ደስ ብሎታል"።

7፥8-9 *አልጸጸትም፤ ብጸጸትም እንኳ ... አሁን ግን ደስ ብሎኛል!* ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የሚያሳዝን ደብዳቤ በመጻፉ በእርግጥ ተጸጽቶአል፤ ነገር ግን የተጸጸተው በጻፈው ደብዳቤ ሳይሆን፣ ደብዳቤውን እንዲጽፍ ባስገደደው ሁኔታ ነው። ከዚህ በላይ ግን የጻፈው ደብዳቤ የተፈለገውን ውጤት ስላስገኘለት ደስ ብሎታል፤ ምክንያቱም ሐዘናቸው ወደ ምሬትና ወደ ጥላቻ ሳይሆን ወደ ንስሐ መርቶአቸዋል። ያዘኑት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ በተጻፈላቸው ደብዳቤ ተጠቀሙ እንጂ አልተጐዱም።

7፥10 *እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ... ዓለማዊ ሐዘን!* እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ንስሐ እንድንገባና በእግዚአብሔር ጸጋ እንድንመላለስ ያደርጋል። ዓለማዊ ሐዘን ግን ሞትን ያመጣል፤ ምክንያቱም ከኀጢአታችን የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት በማዘን ፈንታ፣ ኀጢአታችን ባመጣብን መዘዝ ስለ ራሳችን ማዘን ብቻ ስለሚሆን ነው። የደብዳቤው መሠረታዊ ዐላማ በቆሮንቶስ የነበረውን ቀንደኛ በዳይ ወይም እርሱን የበደለውን ሰው ለመውቀስ ሳይሆን፣ ጳውሎስ ሐዋርያቸው እንደ መሆኑ መጠን ለእርሱ ያላቸውን ታማኝነትና ፍቅር ለመፈተን ነው።

ረገድ አስመስክራችኋል:: 12እንግዲህ እኔ
የጻፍሁላችሁ ስለ በደለው ወይም ስለ ተበደ
ለው ሰው አይደለም፤ ነገር ግን ለእኛ ምን
ያህል ታማኞች እንደ ሆናችሁ፣ በእግዚአብሔር
ፊት ራሳችሁን እንድታዩ በማለት ነው::
13እኛም የተጽናናነው በዚህ ምክንያት ነው::
ከእኛም መጽናናት በተጨማሪ በቲቶ
ደስታ እኛም ይበልጥ ደስ ብሎናል፤ ምክን
ያቱም ሁላችሁም መንፈሱን አሳርፋችኋል::
14በእናንተ ላይ ያለኝ ትምክሕት ለእርሱ
ነግሬው ነበር፤ እናንተም አላሳፈራችሁኝም::
ነገር ግን ስንነግራችሁ የነበረው ሁሉ እው
ነት እንደ ሆነ፣ እንደዚሁም ስለ እናንተ
ለቲቶ በትምክሕት የነገርነው እውነት መሆኑ
ተረጋግጦአል:: 15እርሱም በፍርሀትና በመን
ቀጥቀጥ እንዴት እንደ ተቀበላችሁትና ሁላ
ችሁም እንደ ታዘዛችሁ ሲያስታውስ ለእና
ንተ ያለው ፍቅር እየበረታ ሄዶአል:: 16እኔም
በማናቸውም ነገር ልተማመንባችሁ በመቻሌ
ደስ ብሎኛል::

## የልግስና አስፈላጊነት

8 ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር በመቄዶንያ
ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን
ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን:: 2የደረሰ
ባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታቸው ግን
የላቀ ነበር፤ ድኽነታቸው ብርቱ ቢሆንም
ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር:: 3እንደ ዐቅማ
ቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅማቸው በላይ በፈ
ቃዳቸው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁ::
4እነርሱም ቅዱሳንን ለመርዳት በሚደረገው
አገልግሎት ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ
አጥብቀው ይለምኑን ነበር:: 5እኛ ከጠበቅ
ነው በላይ፣ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ
ሰጡ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸ
ውን ለእኛ ሰጡ:: 6ስለዚህ ቲቶ፣ በእናንተ
መካከል ቀደም ሲል የጀመረውን የልግስና
ሥራ ከፍጻሜ እንዲያደርስ ለምነነው ነበር::
7እናንተም በሁሉ ነገር ይኸውም በእምነት፣
በቃል፣ በዕውቀት፣ በፍጹም ትጋትና ለእኛም
ባላችሁ ፍቅር[ሩ] ልቃችሁ እንደተገኛችሁ፣
በዚህም የቸርነት ሥራ ልቃችሁ እንድት
ገኙ ዐደራ እንላችኋለን::
8ይህን የምለው ትእዛዝ ለመስጠት ብዬ
አይደለም፤ ነገር ግን ሌሎች ከሚያሳዩት
ትጋት አንጻር የፍቅራችሁን እውነተኛነት
ለማረጋገጥ ነው:: 9የጌታችንን የኢየሱስ ክር
ስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤ በእርሱ ድኽ
ነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ
ሀብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድኻ ሆነ::
10ስለዚህ ጉዳይ የምሰጣችሁ ጠቃሚ ምክር
ይህ ነው፤ ባለፈው ዓመት በመስጠት ብቻ
ሳይሆን ለመስጠት በማሰብም ቀዳሚ ነበራ
ችሁ፤ 11አሁንም የጀመራችሁትን ተግባር በዐ
ቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድርሱት፤ ይህም
ለመስጠት የነበራችሁ በጎ ፈቃድ እውን
እንዲሆን ነው:: 12ለመስጠት በጎ ፈቃድ
ካለን ስጦታው ተቀባይነት የሚያገኘው
ባለን መጠን ስንሰጥ እንጂ፣ በሌለን መጠን
ለመስጠት ስንሞክር አይደለም::
13ይህንን የምንለው እናንተ ተቸግራችሁ
ሌሎች ይድላቸው ለማለት ሳይሆን፣ ሁላች
ሁም እኩል እንድትሆኑ ነው:: 14በአሁኑ ጊዜ
የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጉድለት ያሚ
ላል፤ የእነርሱም ደግሞ በተራው የእናን
ተን ጉድለት ያሚላል፤ በዚህም ያላችሁን
እኩል ትካፈላላችሁ:: 15ይህም፣ "ብዙ የሰበ
ሰበ አላተረፈም፤ ጥቂት የሰበሰበም አልጐደ
ለበትም" ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው::

## ቲቶ ወደ ቆሮንቶስ ተላከ

16እኔ ለእናንተ ያለኝን በጎ ሐሳብ በቲቶ

7፥16 2ቆሮ2፥3
8፥1 ሐሥ16፥9
8፥2 ዘፀ36፥5፤2ቆሮ9፥11
8፥3 1ቆሮ16፥2
8፥4 ቍ1፤ሐሥ9:13፤24፥17
8፥6 ቍ10:11:16:17:23፤2ቆሮ2፥13፤12፥18
8፥7 ሮሜ15፥14፤1ቆሮ1፥5፤12፥8፤13፥1:2፤14፥6፤2ቆሮ9፥8
8፥8 1ቆሮ7፥6
8፥9 ማቴ20፥28፤ሮሜ3፥24፤2ቆሮ6፥10፤13፥14፤ፊል2፥6-8
8፥10 1ቆሮ7፥25:40፤16፥2:3፤2ቆሮ9፥2
8፥11 ቍ12:19፤ዘፀ25፥2፤2ቆሮ9፥2
8፥12 ማር12፥43:44፤2ቆሮ9፥7
8፥14 ሐሥ4፥34፤2ቆሮ9፥12
8፥15 ዘፀ16፥18
8፥16 2ቆሮ2፥13:14፤ራእ17፥17

ሩ7 *አንዳንድ ቅጆች ለእናንተ ባለን ፍቅር ይላሉ*

*8፥1-9፥15፤* ጳውሎስ ይህን የጻፈው በኢየሩሳሌም የሚገኙ ክርስቲያኖች ለደረሰባቸው ችግር የቆሮንቶስ ሰዎች ማሰባሰብ ጀምረው የነበረውንና ያልጨረሱትን የገንዘብ መዋጮ ጉዳይ ከዳር እንዲያደርሱት ለማሳሰብ ነው::

8፥1 *ጸጋ፤* የእማኞች፣ "የቸርነት ሥራ" (ቍ7) ራሱን ለሌሎች አሳልፎ ከሰጠው፣ "ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ" (ቍ9) አይበልጥም::

8፥2 *ደስታቸው ... የላቀ፤* ደስ የተሰኙት ከወንጌል ባገኙት በረከት ነው::

8፥5 *በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፤* እውነተኛ ክርስቲያናዊ ስጦታ የሚጀምረው ራስን ከመስጠት ነው:: እነዚህ የመቄዶንያ ክርስቲያኖች በቆሮንቶስ ለነበሩ አማኞችና በየትኛውም ዘመን ለምትገኝ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጸጋ በሕዝቡ ላይ የሚያመጣውን ታላቅ ለውጥ በማሳየት ረገድ ትልቅ ምሳሌ መሆናቸውን አሳይተዋል:: የዚህም ደብዳቤ መሪ ሐሳብ ይኸው ነው (ከ 12፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥6 *ቲቶ... ለምነነው ነበር፤* ከዓመት በፊት የተጀመረው የርዳታ ገንዘብ የማሰባሰቡ ተግባር ይመራ የነበረው በቲቶ ነበር (ቍ10፤ 9፥2 ይመ)፤ ይሁን እንጂ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ሂደቱ ሳይደክም ወይም ሳይቋረጥ እንደ ቀረ ምንም ጥርጥር የለውም:: ስለዚህ ጳውሎስ ይህንን በጎ ሥራ ከፍጻሜ ያደርሱ ዘንድ፣ ቲቶ ይህን መልእክት ይዞ እንዲሄድ ይልከዋል (በቍ1-5 ባለው ክፍል በእግዚአብሔር ጸጋና በልግስና በሰጡት በመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን ግንኙነት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥7 *በሁሉ ነገር... ልቃችሁ፤* ከ1ቆሮ1፥4-7 ጋር ያነጻጽሩ::

8፥8 *ትእዛዝ ለመስጠት ብዬ አይደለም፤* እውነተኛ ቸርነትና ልግስና ትእዛዝ በመስጠት የሚፈጸም አይደለም:: *የፍቅራችሁ እውነተኛነት፤* ይህን ማረጋገጥ የሚችሉት በልግስናና በማንኛውም ጊዜ በመስጠት ነው:: *ሌሎች ... ትጋት፤* የመቄዶንያን አብያተ ክርስቲያናት መልካም ምሳሌነት ያመለክታል (ቍ1-5)::

8፥9 *ሀብታም ሆኖ ሳለ ... ድኻ ሆነ፤* የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በመምጣና በእኛም ምትክ ራሱን ቤዛ አድርጎ በሰጠ ጊዜ፣ ከዚያ ታላቅ ክብሩ ራሱን ዝቅ በማድረግ አዋረደ (ፊል2፥7 ይመ):: *በእርሱ ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ፤* ክርስቲያኖች በልግስና መስጠትን እንዲማሩ የሚያነሣሣ እውነታ ነው::

8፥11 *አሁንም ... ከፍጻሜ እንድታደርሱት፤* 'ባለፈው ዓመት' (ቍ10) በፈቃደኛነት የተጀመረው በጎ ሥራ ከፍጻሜ መድረስ አለበት (የቍ6 ማብ ይመ)::

8፥12 *ባለን መጠን፤* የምንሰጠው ነገር ምንም ያህል ጥቂት ቢሆን፣ ከእኛ የሚፈለገው በልግስና ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ መገኘቱ ነው:: እዚህ ላይ ይህን መርሕ በሥራ ላይ በማዋሏ ትልቅ ምሳሌ የምትሆነን ድኻዋ መበለት ናት (ማር12፥41-44 ይመ):: በቆሮንቶስ የርዳታው ገንዘብ እንዴት መሰብሰብ እንዳለበት ጳውሎስ ሐሳብ ያቀረበው በመጀመሪያ መልእክቱ ነበር (1ቆሮ16፥1-2 ይመ)::

*8፥15፤* ጥቅሱ የሚያወሳው እስራኤላውያን በምድረ በዳ መና ስለመሰብሰባቸው ነው::

8፥16 *ቲቶ፤* ከቆሮንቶስ ሰዎች ጋር በታማኝነትና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመፍጠር ችሎአል (7፥6-7፡13-15 ይመ):: ባለፈው ዓመት ገንዘብ የማሰባሰቡ ተግባር ሲጀምር አመ

ልብ ውስጥ ያኖረ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤
17ምክንያቱም ቲቶ ወደ እናንተ የመጣው
ልመናችንን በመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ በታ
ላቅ ጕጕትና በራሱ ፈቃድ በመነሣሣት
ነበር። 18ከእርሱም ጋር በወንጌል ስብከት
በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን
ወንድም ልከነዋል። 19ከዚህም በላይ ስጦታ
ውን በምንወስድበት ጊዜ አብሮን እንዲሄድ
በአብያተ ክርስቲያናት ተመርጦአል፤ ስጦ
ታውንም የምንወስደው ጌታን ራሱን ለማክ
በርና ሌሎችን ለመርዳት ካለን በጎ ፈቃድ
የተነሣ ነው። 20በዚህ በምናከናውነው የቸር
ነት ሥራ አንዳች ነቀፋ እንዳይገኝብን እንጠ
ነቀቃለን። 21ምክንያቱም ዐላማችን በጌታ ፊት
ብቻ ሳይሆን፣ በሰውም ፊት መልካም የሆነ
ውን ነገር ማድረግ ነው።

22ደግሞም ብዙ ጊዜ በብዙ መንገድ ተፈ
ትኖ ትጉ ሆኖ የተገኘውን ወንድማችንን
ከእነርሱ ጋር ልከነዋል፤ አሁንም በእናንተ
እጅግ ከመታመኑ የተነሣ ከመቼውም ጊዜ
ይልቅ እየተጋ ነው። 23ስለ ቲቶ የሚጠይቅ
ቢኖር፣ እርሱ እናንተን ለማገልገል አብሮኝ
የሚሠራ ባልደረባዬ ነው፤ ስለ ወንድሞ
ቻችንም የሚጠይቅ ቢኖር እነርሱ የአብ
ያተ ክርስቲያናት ተወካዮችና የክርስቶስ
ክብር ናቸው። 24ስለዚህ የፍቅራችሁን እው
ነተኛነትና በእናንተም የምንታመነው የቱን
ያህል እንደ ሆነ በአብያተ ክርስቲያናት
ፊት ግለጡላቸው።

9 ለቅዱሳን ስለሚደረገው አገልግሎት ል
ጽፍላችሁ አያስፈልግም። 2ምክንያቱም
ሌሎችን ለመርዳት ያላችሁን በጎ ፈቃድ
ዐውቃለሁ፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ እናንተ
በአካይያ የምትኖሩ ሌሎችን ለመርዳት
ዝግጁ እንደ ሆናችሁ ለመቄዶንያ ሰዎች
አፌን ሞልቼ ተናግሬአለሁ፤ ቅን ፍላጎታ
ችሁም ብዙዎችን ለበጎ ሥራ አነሣሥቶ
አል። 3እንግዲህ በዚህ ነገር በእናንተ ላይ
ያለን ትምክሕት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር
አስቀድሞ ስለ እናንተ እንደ ተናገርሁት
ተዘጋጅታችሁ እንድትገኙ ወንድሞችን ልኬ
አለሁ። 4ምናልባት የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ
ጋር መጥተው ሳትዘጋጁ ቢያገኟችሁ፣ እና
ንተ ብቻ ሳትሆኑ እኛም ያን ያህል በእና
ንተ በመመካታችን እናፍራለን። 5ስለዚህ
ወንድሞች አስቀድመው ወደ እናንተ እንዲ
መጡና ከዚህ በፊት ለመስጠት ቃል የገባ
ችሁትን ስጦታ አጠናቃችሁ እንድትጠብ
ቋቸው፣ እነርሱን መለመን አስፈላጊ ሆኖ
አግኝቻለሁ፤ እንግዲህ በልግስና ለመስጠት
ያሰባችሁት ነገር በግዴታ ሳይሆን በፈቃደ
ኝነት የተዘጋጀ ይሆናል።

## በልግስና መስጠት

6ይህን አስታውሱ፤ ጥቂት የዘራ ጥቂት
ያጭዳል፤ ብዙ የዘራ ብዙ ያጭዳል። 7እያ
ንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይ
ሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክን
ያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው
ይወዳል። 8ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈል
ጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ
እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን ሁሉ ሊያ
በዛላችሁ ይችላል፤ 9ይህም፣

"በተነ፤ ለድኾችም ሰጠ፤
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል"
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።

10ለዘሪ ዘርን፣ ለመብላት እንጀራን የሚ
ሰጥ እርሱ የምትዘሩትን አትረፍርፎ ይሰጣ
ችኋል፤ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያበዛላችኋል።
11ሁልጊዜ በልግስና መስጠት እንድትችሉ
በሁሉ ነገር ያበለጽጋችኋል፤ ልግስናችሁም
በእኛ በኩል የሚደርሳቸው ሰዎች እግዚአብሔ
ርን ለማመስገን ምክንያት ይሆናቸዋል።

12ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳ
ንን ጕድለት የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ
ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ነው።
13የክርስቶስን ወንጌል ተቀብላችሁ ስለ ታዘ
ዛችሁና ለእነርሱም ሆነ ለሌሎች ስላሳያ
ችሁት ልግስና ሰዎች ተፈትኖ ስላለፈው
አገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ 14ስለ
እናንተም በሚጸልዩበት ጊዜ እግዚአብሔር
ከሰጣችሁ ታላቅ ጸጋ የተነሣ ይናፍቋች

8፥17 ቍ6
8፥18 1ቆሮ7፥17፤ 2ቆሮ2፥12፤12፥18
8፥19 ቍ11፡12፤ ሐሥ14፥23፤1ቆሮ 16፥3፡4
8፥21 ሮሜ12፥17፤ 14፥18፤ቲቶ2፥14
8፥23 ቍ18፡22፤ 2ቆሮ2፥13፤ፊል2፥25፤ ፊሞ17
8፥24 2ቆሮ7፥4፡ 14፤9፥2
9፥1 ሐሥ9፥13፤24፥ 17፤1ተሰ4፥9
9፥2 ሐሥ18፥12፤ 2ቆሮ7፥4፡14፤8፥10፡ 11፡12፡19፡24
9፥3 1ቆሮ16፥2፤ 2ቆሮ8፥23
9፥4 ሮሜ15፥26
9፥5 ቍ3፤2ቆሮ 12፥17፡18፤ፊል4፥17
9፥6 ምሳ11፥24፡25 ፤22፥9፤ገላ6፥7፡9
9፥7 ዘፀ25፥2፤ዘዳ 15፥10፤ሮሜ12፥8 ፤2ቆሮ8፥12
9፥8 ኤፌ3፥20፤ ፊል4፥19
9፥9 መዝ112፥9፤ ሚል3፥10
9፥10 ኢሳ55፥10፤ ሆሴ10፥12
9፥11 ቍ5፤1ቆሮ1፥ 5፤2ቆሮ1፥11፤4፥15
9፥12 2ቆሮ1፥11፤ 8፥14
9፥13 ቍ5፤ማቴ
9፥8 ፤2ቆሮ2፥12፤ 8፥4፤ዕብ3፥1

ራር ሰጥቶአል (የቍ6 ማብ ይመ)።

8፥18 *ወንድም፤* ምናልባት ሉቃስን አሊያም በርናባስን ሊሆን ይችላል፤ ያም ሆነ ይህ በታማኝ አገልጋይነቱ በጣም የታወቀ ሰው ነው።

8፥19 *በአብያተ ክርስቲያናት ተመርጦአል፤* የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በገንዘብ አያያዝ ረገድ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጳውሎስ መልካም ምሳሌን ትቶላቸዋል።

*8፥20፤* አንድ ሰው የጌታን ሥራ የሚሠራው ትክክለኛና እውነተኛ በሆነ መንገድ መሆኑን፣ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ሰዎችም እንዲያዩት ያስፈልጋል (ከቍ19-21 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥21 *ዐላማችን ... መልካም የሆነውን ማድረግ ነው፤* ጳውሎስ በመካከላቸው የተመላለሰው በዚህ ዐይነት ቢሆንም፣ ስሙን የሚያጠፉት ሰዎች ግን አሁንም አልተኙለትም (12፥17-18 እንዲሁም የመጽሐፉን መግቢያ ይመ)፤ ይሁን እንጂ እርሱ የላካቸው ሰዎች ያሳዩት ታማኝነት የእርሱን ታማኝነት የሚያሳይ ነበር (የቍ23 ማብ ይመ)።

8፥22 *ወንድማችን፤'* ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው ወንድም (ቍ18 እና ማብ ይመ)፣ የዚህም ወንድም ማንነት በውል አይታወቅም።

8፥23 *አብሮኝ የሚሠራ ባልደረባዬ፤* የ2፥13 ማብ ይመ። በትክክለኛው መንገድ ተመርጠው አብያተ ክርስቲያናትን እንዲወክሉ የተላኩ ናቸው (ስለዚህ ጳውሎስ ብቻ መርጦ እንደሾማቸው በመቍጠር ሊሻሩ አይችሉም)። የሐሥ 20፥4 ማብ ይመ። *የክርስቶስ ክብር፤* በታማኝነታቸው የታወቁ ክርስቲያኖች ናቸው።

*9፥6፤* በጣም የታወቀ ምሳሌያዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ከብሉይ ኪዳኑ መጽሐፈ ምሳሌ የተወሰደ አይደለም።

*9፥7፤* ሉቃ 6፥38 ይመ።

9፥8 *በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ፤* እግዚአብሔር ከተትረፈረፈው ጸጋ የተነሣ እያንዳንዱ ክርስቲያን በልግስና አትረፍርፎ እንዲሰጥ ያስችለዋል (ቍ11 ይመ)

9፥9-10 *የጽድቃችሁም፤* የመዝ 1፥5 ማብ ይመ።

9፥12 *የቅዱሳንን ጕድለት የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን፤* የቆሮንቶስ ሰዎች በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ክርስቲያኖች ያደረጉት ልግስና፣ ከኢየሩሳሌም ዐልፎ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከመታወቁም በላይ በየስፍራው የሚገኙ ቅዱሳን ለጸሎትና ለምስጋና እንዲነሣሡ አድርጎአል (ቍ13-14)።

9፥14 *እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ታላቅ ጸጋ የተነሣ፤* በብርቱ ችግር ላይ ይገኙ የነበሩ ወንድሞቻቸውን ከልብ ለመርዳት

ኋል:: [15]በቃላት ሊገለጥ ስለማይቻል ስጦ
ታው እግዚአብሔር ይመስገን::

### ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ያቀረበው መከላከያ

**10** እኔ ጳውሎስ፣ በእናንተ ፊት ስሆን
"ዐይነ ዐፋር"፣ ከእናንተ ስርቅ ግን፣
"ደፋር" የተባልሁ በክርስቶስ የዋህ
ነትና ገርነት እለምናችኋለሁ:: [2]ወደ እና
ንተ በምመጣበት ጊዜ በዓለማዊ መንገድ
እንደምንኖር አድርገው በሚቈጥሩን ሰዎች
ላይ በድፍረት ለመናገር ቈርጫለሁ፤ እናን
ተን ግን በዚያ ዐይነት ድፍረት እንድናገር
እንዳታደርጉኝ እለምናችኋለሁ:: [3]የምንኖረው
በዚህ ዓለም ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም
ስልት አይደለም:: [4]ደግሞም የምንዋጋበት
የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደ
ለም፤ ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ
የሚችል መለኮታዊ ኀይል ያለው ነው::
[5]በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነ
ሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈር
ሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስ
ቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን:: [6]መታዘዛ
ችሁ በተፈጸመ ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ
ለመቅጣት ተዘጋጅተናል::

9፥15 ሮሜ5፥15:16 12ቆሮ2፥14
10፥1 ማቴ11፥29 ፤ገላ5፥2፤ኤፌ3፥1
10፥2 ሮሜ12፥2፤ 1ቆሮ4፥21
10፥3 ቍ2
10፥4 ቍ8፤ኤር1፥10፤23፥29፤1ቆሮ2፥5፤ 2ቆሮ6፥7:13፥10
10፥5 ኢሳ2፥11:12 ፤1ቆሮ1፥19፤2ቆሮ 9፥13
10፥6 2ቆሮ2፥9፤ 7፥15
10፥7 ዮሐ7፥24፤ 1ቆሮ1፥12፤3፥23፤14 ፥37፤2ቆሮ5፥12፤ 11፥23
10፥8 ቍ4:13:15 ፤ኤር1፥10፤2ቆሮ 13፥10
10፥10 ቍ1፤1ቆሮ 1፥17፤2፥3፤2ቆሮ11፥ 6፤ገላ4፥13:14
10፥12 ቍ18፤ 2ቆሮ3፥1
10፥13 ቍ15:16፤ ሮሜ12፥3

[7]እናንተ የምትመለከቱት ውጫዊውን ነገር
ብቻ ነው::[ሀ] ማንም የክርስቶስ በመሆኑ ቢመካ
እርሱ የክርስቶስ እንደ ሆነ ሁሉ እኛም
የክርስቶስ መሆናችንን ሊገነዘብ ይገባዋል::
[8]ጌታ በሰጠን ሥልጣን እጅግ ብመካም
በዚህ አላፍርም፤ ሥልጣኑን የተቀበልነው
እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለ
ምና:: [9]በመልእክቶቼ የማስፈራራችሁ አይ
ምሰላችሁ:: [10]አንዳንዶች፣ "መልእክቶቹ ከባ
ድና ጠንካራ ናቸው፤ ነገር ግን ሰውነቱ ሲታይ
ደካማ፣ ንግግሩም የተናቀ ነው" ይላሉ:: [11]እን
ዲህ የሚሉ ሰዎች በሩቅ ሆነን በመልእክታ
ችን የምንናገረውን ሁሉ በቅርብ ሆነን በተግ
ባራችን የምንገልጸውም እንደዚያው መሆ
ኑን መገንዘብ አለባቸው::

[12]ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋር ራሳ
ችንን ልንመድብ ወይም ልናነጻጽር አንደ
ፍርም፤ እነርሱ ራሳቸውን በራሳቸው ሲመ
ዝኑና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያነጻ
ጽሩ አስተዋዮች አይደሉም:: [13]እኛ ግን ከመ
ጠን በላይ አንመካም፤ የምንመካው እግዚ
አብሔር በመደበልንና እስከ እናንተም እንኳ
በሚደርሰው የአገልግሎታችን ወሰን ነው::

[ሀ]7 ወይም *ግልጥ የሆነውን እውነታ ብቻ ነው*

በሳዩት ቅንነት ውስጥ ገልጠውታል::

9፥15 *በቃላት ሊገለጥ ስለማይቻል ስጦታው፤* የገዛ ልጁን (ዮሐ3፥16 ) ነው:: የመጀመሪያው ሰጭ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱም በመጀመሪያ በልጁ አማካይነት ራሱን ሰጠን፤ ይህም እውነተኛ ክርስቲያናዊ ስጦታ ለዚህ በቃላት ሊገለጥ ስለማይችለው የእግዚአብሔር ስጦታ የምናቀርበው ምላሽ ነው (ከ 8፥9፤ 1ዮሐ 4፥9-11 ጋር ያነጻጽሩ)::

10፥1 *በእናንተ ፊት ስሆን "ዐይነ ዐፋር" ... ስርቅ ግን "ደፋር"፤* ከመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች ድምፀት እንደምንረዳው ከሆነ፣ በርካታ የቆሮንቶስ አማኞች በጳውሎስ ተቃዋሚዎች ተታለው ከተወሰዱ በኋላ እንደ ገና ወደ ጳውሎስ ሳይመለሱ አልቀረም (ከ7፥6-13 ጋር ያነጻጽሩ):: በዚህ በመጨረሻው ክፍል ደግሞ (ም10-13)፣ ጳውሎስ ስሙን ካጠፉት ተቃዋሚዎቹ ጋር ፊት ለፊት ሲጋጠም ይታያል:: አገልግሎቱ ተቀባይነት እንዲያጣ የሚመኙት ተቃዋሚዎቹ ከሩቅ ሆኖ ሲናገር ደፋር ይመስላል፤ በተለይ በመልእክቶቹ (በ1ቆሮ4፥18-21 ላይ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ "በትር ይዤ ልምጣን?" በማለት ከተናገረው ጋር ያነጻጽሩ) ከባድ የሥነ ሥርዐት እርምጃ ለመውሰድ እንደቈረጠ ሰው ይዝታል እያሉ ይናገሩ ነበር:: ይሁን እንጂ በአካል በመካከላቸው ቢገኝ እዚህ ግባ የሚባል ሰው እንዳልሆነና ይልቁንም ደካማና ወላዋይ ሰው መሆኑን ይናገሩ ነበር፤ ባጭሩ አለኝ የሚለው የሐዋርያነት ሥልጣን እንኳ የለውም ይሉ ነበር:: ጳውሎስ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ ሁኔታው የሚፈቅድለት ከሆነ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ነው (ቍ6:10-11 ይመ):: የክርስቶስን የዋህነትና ገርነት መጥቀሱም በመካከላቸው በሚገኝበት ጊዜ እነዚህን ባሕርያት ለማሳየት ትልቅ ምኞት ያለው መሆኑን ነው:: ያም ሆነ ይህ ከመልእክቱ እንደምንረዳው፣ ጳውሎስ በራሱ ደካማ ቢሆንም በጌታ ግን ብርቱ ነው፤ እነዚያም ዐመፀኞች ለእርሱ የተሰጠውን መለኮታዊ ሥልጣን በተግባር ያያሉ::

10፥4 *የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ፤* ጳውሎስ ለፍልሚያ ተዘጋጅቶአል፤ ሆኖም እርሱ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች በዚህ በወደቀው ዓለም ዘንድ ዕጹብ ድንቅ የተባሉና በሰዎች ትዕቢትና እብሪት የተመሠረቱ አይደሉም:: *ምሽግ፤* "በእግዚአብሔር ዕውቀት" (ከሮሜ 1፥18-23 ጋር ያነጻጽሩ) ላይ በግልጽ የተነሣ "ክርክርና ከንቱ ሐሳብ" (ቍ5) ነው፤ ይህም ሐሰተኞች ሐዋርያት ከንቱ በሆነ ሐሳብ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን እምነት ለመናድ ታጥቀው የተነሡበት ስልት ነው (1ቆሮ2፥13-14 ይመ)::

10፥5 *አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ፤* የሰው ሁለንተና ለክርስቶስ ጌትነት የተገዛ ይሆናል::

10፥7 *እርሱ የክርስቶስ እንደ ሆነ* የክርስቶስ ወገን ነን በማለት በመንፈሳዊነታቸው የሚመኩትንና (1ቆሮ 1፥12) በቆሮንቶስ የነበሩ ሐሰተኞች ሐዋርያት የተናገሩትን የሚያንጸባርቅ ነው:: በሚያስደንቅ መንገድ ከጌታ ጋር የተገናኘውና ከሙታን የተነሣው ጌታ የሾመው (ሐሥ9፥3-9፤ 22፥6-11፤ 26፥12-18 ይመ) እንዲሁም የሚሰብከውን ወንጌል፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ የገለጠለት" (ገላ 1፥11፤ ከ2ቆሮ 12፥2-7 ጋር ያነጻጽሩ) ጳውሎስ እርሱም የክርስቶስ ወገን እንደሆነ በግልጽ ይናገራል::

10፥8 *ሥልጣኑን ... እናንተን ለማነጽ፤* የጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣን መሠረታዊ ዐላማ ለመገንባት ይኸውም ለማነጽ እንጂ ለመናድ ወይም ለማፍረስ አይደለም (ይሄው አባባል በ13፥10 ላይ እንደ ገና ተወስቶአል):: በመልእክቱ ላይ ያነሣቸው ጥያቄዎች የጠፋውን ነገር የሚያቀኑና ወደ ቆሮንቶስ ሲሄድ ነገሮች እንዲስተካከሉ የሚያደርጉ ናቸው:: ይህም ለመውሰድ ያሰበውን ከባድ ርምጃ (ለማፍረስ የተባለውን) የሚያስቀርና እነርሱ የሚታነጹበትን ነገር (ለማነጽ የተባለውን) የሚያመጣ ነው::

10፥9 *በመልእክቶቼ የማስፈራራችሁ፤* 2፥3-4፤ 7፥8-9፤ ም10-13፤ 1ቆሮ 4፥18-21 ይመ::

10፥10 *ንግግሩም የተናቀ፤* የቍ1 ማብ ይመ:: የጳውሎስ ተቃዋሚዎች ርቱዕ አንደበትን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ግልብ ሰዎችን ይበዘብዙ ነበር:: የጳውሎስ ንግግር ግን ከዚህ ፍጹም የተለየ ነበር፤ ይኸውም ንግግሩ ግልጽና ቀጥተኛ እንዲሁም አስመሳይነትም ሆነ ክፍያን የማይጠይቅ ነበር (የ11፥7 ማብ ይመ)፤ በመሆኑም ስሙን የሚያጠፉት ተቃዋሚዎቹ የሚናገሩት ነገር ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ንግግሩ ሁሉ ከንቱ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው:: ጳውሎስ ግን ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ የንግግር ችሎታንና ጥበብን ወደ ጐን በመተው የተሰቀለውን ክርስቶስን ብቻ ለመስበክ ወስኖ ነበር፤ የተለወጠውም የቆሮንቶስ አማኞች ሕይወት ጳውሎስ ይሰብክ የነበረው በመለኮታዊ ኀይል እንደሆነ ምስክር ነው (ከ1ቆሮ2፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ)::

10፥12 *ራሳቸውን በራሳቸው ሲመዝኑና፤* በቆሮንቶስ የነበሩ ሐሰተኞች መምህራን ከእነርሱ በቀር ሌላ መለኪያ እንደሌለ አድርገው ራሳቸውን ይመለከቱ ነበር፤ ጳውሎስ ይመካ የነበረው ግን በጌታ ብቻ ነበር (ቍ13-18 ይመ፤ ከ1ቆሮ 1፥31 ጋር ያነጻጽሩ)::

10፥13 *እግዚአብሔር በመደበልንና ... ወሰን፤* ጳውሎስ ይህን የተናገረው በሩጫ ውድድር ላይ፣ ለሚፎካከሩ ሰዎች የተከለለውን ድንበር እያሰበ ሊሆን ይችላል:: በዚህም መሠረት፣ "ክልል" ሲባል፣ "ድንበር የተበጀለት ጠባብ መንገድ" ወይም "የሥራ መስክ" (ቍ15) ወይም "አካባቢ" (ቍ16) ማለት ነው:: ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሠርገው የገቡት ሐሰተኞች መምህራን ለጳውሎስ ተወስኖ የተሰጠውን ክልል ጥሰዋል፤ ይህንን ክልል ለጳውሎስ ለይቶ የሰጠውና እውነተኛ ሐዋርያ አድርጎ ወደ ቆሮንቶስ

14የክርስቶስን ወንጌል ይዘን ወደ እናንተ
በመጣን ጊዜ፣ ከተመደበልን የአገልግሎት
ወሰን አላለፍንም::[ሀ] 15ደግሞም ሌሎች በደከ
ሙበት ሥራ ከመጠን በላይ በመመካት
ከተመደበልን ወሰን አናልፍም፤ ይልቁንም
እምነታችሁ እያደገ በሄደ ቍጥር በእናንተ
ዘንድ የተመደበልን አገልግሎት እየሰፋ
እንደሚሄድ ተስፋ እናደርጋለን:: 16ስለዚህ
በሌላው ሰው ክልል አስቀድሞ በተሠራ ሥራ
ሳንመካ፣ ከእናንተ ወዲያ ባለው አገር ወን
ጌልን መስበክ እንችላለን:: 17ነገር ግን፣
"የሚመካ በጌታ ይመካ"፤ 18ምክንያቱም ጌታ
ራሱ የሚያመሰግነው እንጂ፣ ራሱን በራሱ
የሚያመሰግን ተቀባይነት አይኖረውም::

## ጳውሎስና ሐሰተኞች ሐዋርያት

11 ጥቂቱን ሞኝነቴን እንደምትታገሡኝ
ተስፋ አደርጋለሁ፤ በእርግጥም እየታ
ገሣችሁኝ ነው:: 2በእግዚአብሔር ቅናት እቀና
ላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት ድንግል
ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል አጭቻች
ኋለሁና:: 3ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተን
ኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም
ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና
ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ:: 4ምክንያ
ቱም አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ እኛ
ከሰበክንላችሁ ኢየሱስ ሌላ ኢየሱስ ቢሰብ
ክላችሁ፣ ወይም ከተቀበላችሁት መንፈስ
የተለየ መንፈስ ብትቀበሉ ወይም ከተቀበ
ላችሁት ወንጌል የተለየ ወንጌል ብትቀበሉ፣
ነገሩን በዝምታ ታልፉታላችሁ ማለት ነው::
5እኔ ግን "ታላላቅ ሐዋርያት" ከሚባሉት
በምንም የማንስ አይመስለኝም:: 6የንግግር
ችሎታ ባይኖረኝም እንኳ፣ ዕውቀት ግን
አለኝ፤ ይህንንም በሁሉ መንገድ በሚገባ
ግልጽ አድርገንላችኋል::

7እናንተ ከፍ እንድትሉ ራሴን ዝቅ አድ
ርጌ የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ዋጋ ለእናንተ
መስበኬ እንደ ኀጢአት ተቈጥሮብኝ ይሆን?
8እናንተን ለማገልገል ስል ከሌሎች አብያተ
ክርስቲያናት ርዳታ በመቀበሌ እነርሱን ዘር
ፌአቸዋለሁ:: 9ከእናንተም ጋር ሳለሁ እንዳች
ባስፈለገኝ ጊዜ፣ ከመቄዶንያ የመጡ ወን
ድሞች የሚያስፈልገኝን ስለሰጡኝ ለማንም
ሸክም አልሆንሁም:: በእናንተ ላይ በምንም
ነገር ሸክም እንዳልሆን ተጠንቅቄአለሁ፤ ወደ
ፊትም እጠነቀቃለሁ:: 10የክርስቶስ እውነት
በውስጤ እስካለ ድረስ፣ በአካይያ አውራጃ
ይህን ትምክሕቴን ማንም ሊገታው አይች
ልም:: 11ይህን የምለው ለምንድን ነው? ስለ
ማልወዳችሁ ነውን? እንደምወዳችሁ እግዚ
አብሔር ያውቃል:: 12ከእኛ ጋር እኩል ለመ
ሆን በሥራቸው እየተመኩ ቀን የሚጠብቁ
ትን ሰዎች ምክንያት ለማሳጣት አሁን የማ
ደርገውን ወደፊትም አደርጋለሁ::

13እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋ
ርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋወጡ፣

[ሀ]13-15 ወይም 13 እኛ ግን ከመጠን በላይ ስለሆኑ ነገሮች አንመካም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በመደበልንና እስከ እናንተም እንኳ በሚደርሰው እንመካለን:: 14…15 ደግሞ ሌሎች በሠሩት ሥራ ከመጠን በላይ ስለሆኑ ነገሮች አንመካም፤

10፥14 1ቆሮ3፥6፤ 2ቆሮ2፥12
10፥15 ቍ13፤ሮሜ 15፥20፤2ተሰ1፥3
10፥16 ሐሥ19፥21 ፤ሮሜ1፥1፤2ቆሮ2፥12
10፥17 መዝ34፥2፤ 44፥8፤ኤር9፥24፤ 1ቆሮ1፥31
10፥18 ቍ12፤ሮሜ 2፥29
11፥1 ቍ4:16:17 :19:20:21፤ማቴ17፥ 17፤2ቆሮ5፥13
11፥2 ሆሴ2፥19፤ 2ቆሮ4፥14፤ኤፌ5፥26 :27
11፥3 ዘፍ3፥1-6:13 ፤1ጢሞ2፥14፤ራእ 12፥9
11፥4 ቍ1፤ሮሜ 8፥15፤1ቆሮ3፥11፤ገላ 1፥6-9
11፥5 2ቆሮ12፥11 ፤ገላ2፥6
11፥6 1ቆሮ1፥17፤ 2ቆሮ8፥7፤ኤፌ3፥4
11፥7ሮሜ1፥1፤1ቆሮ 9፥18፤2ቆሮ12፥13
11፥8 ፊል4፥15:18
11፥9 2ቆሮ12፥13 :14:16፤ፊል4፥15:18
11፥10 ሐሥ18፥12 ፤ሮሜ9፥1፤1ቆሮ9፥15
11፥11 ቍ31፤ሮሜ 1፥9፤2ቆሮ12፥15
11፥13 ማቴ7፥15፤ ቲቶ1፥10፤ራእ2፥2

ሰዎች የላከው እግዚአብሔር ነው::

10፥16 *ወዲያ ባለው አገር፤* ይህን የተናገረው እስፔንን እያሰበ ሊሆን ይችላል (ሮሜ 15፥24፡ 28 ይመ)::

11፥1 *ሞኝነቴን፤* ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን ከወረሩት ሐሰተኞች መምህራን ጋር የእርሱን አገልግሎት ለማወዳደር ስለ ራሱ መናገር ነበረበት፤ ይህም እንደ ሞኝነት የሚቈጠር ትምክህት ነበር::

11፥2 *በእግዚአብሔር ቅናት፤* ጳውሎስ ክርስቶስንና ወንጌሉን ለሚቀናቀን ሐሳብ ከቶ አይተኛም:: *ለአንድ ባል … አጭቻችኋለሁ፤* ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞች መንፈሳዊ አባት እንደ መሆኑ መጠን (ከ6፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ ሙሽራ ሆኖ ለቀረበው ለክርስቶስ ሲያጫቸው ይታያል፤ ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ ሙሽራ እንደ ሆነች ተወስቶአል (ማቴ9፥15፤ ዮሐ3፥29፤ ሮሜ7፥4፤ 1ቆሮ6፥15፤ ኤፌ5፥23-32፤ ራእ19፥7-9፤21፥2):: *ንጽሕት ድንግል፤* በሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ያልተበከለች ማለት ነው (ቍ3-4 ይመ)::

11፥4 *እኛ ከሰበክንላችሁ ሌላ ኢየሱስ፤* ሐሰተኞች መምህራን በአይሁድ አመለካከት የተቀረጸውን ሌላ ኢየሱስ ይሰብኩ ነበር (የጳውሎስ ተቃዋሚዎች አይሁድ ነበሩ፤ ቍ22 ይመ):: *የተለየ መንፈስ፤* የነጻነት፣ የፍቅር፣ የደስታ፣ የሰላምና የኀይል መንፈስ ሳይሆን (ከ 3፥17፤ ሮሜ 14፥17፤ ገላ 2፥4፤ 5፥1:22፤ ኤፌ 3፥20፤ ቈላ 1፥11፤ 2ጢሞ 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ) የባርነት፣ የፍርሀትና የዓለማዊነት መንፈስ (ከሮሜ 8፥15፤ 1ቆሮ 2፥12፤ ገላ 2፥4፤ 4፥24፤ ቈላ 2፥20-23 ጋር ያነጻጽሩ) ነው:: *የተለየ ወንጌል፤* ከገላ 1፥6-9 ጋር ያነጻጽሩ:: *በዝምታ ታልፉታላችሁ፤* የቆሮንቶስ አማኞች በመካከላቸው እንደ ፈለጉ የሚፈነጩትን አታላዮች ዝም ብለዋቸዋል::

11፥5 *"ታላላቅ ሐዋርያት"፤* እዚህ ላይ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሠርገው የገቡትን ሐሰተኞች መምህራን በምፀት እየተናገረ ነው፤ እነርሱም ራሳቸውን እየካቡ በእብሪት ከመናገራቸው በስተቀር በእርግጥ እውነተኛ ሐዋርያት አይደሉም (ከ10፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥6 *የንግግር ችሎታ ባይኖረኝም፤* የረቀቀ የንግግር ችሎታንም ሆነ ርቱዕ አንደበትን አልተጠቀምሁም ማለቱ ነው (የ 10፥10 ማብ ይመ):: *ዕውቀት ግን አለኝ፤* የቆሮንቶስ አማኞች በሚገባ እንደሚያውቁት፣ ጳውሎስ እውነተኛ፣ ብርቱና ከእግዚአብሔር የተሰጠ የክርስቶስ ዕውቀት ነበረው፤ ይህም ዕውቀት ሐሰተኞች መምህራን እነርሱን ለማታለል ከሚጠቀሙበት ከነይል አልባ ምድራዊ ጥበብ ጨርሶ የተለየ ነው (ከ1ቆሮ 2፥6-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥7 *ያለ ዋጋ፤* ጳውሎስ ለሚያስተምረው ትምህርት ክፍያ አለመቀበሉ፣ የትምህርቱን ከንቱነት ያሳያል በማለት ተቃዋሚዎቹ የሚያቀርቡበት ሌላው ትችት ነው:: ያቀረቡት ትችት ስስታምነታቸውን ለመሸፋፈን ረድቶአቸዋል፤ ምክንያቱም በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የነበሩ ፈላስፎችና የሃይማኖት መምህራን በየአገሩ እየዞሩ ሲያስተምሩ ክፍያን እንደሚጠይቁ፣ እነርሱም ለሚሰጡት አገልግሎት ክፍያን ይጠይቁ ነበር:: የጳውሎስ ተቃዋሚዎች አንድ መምህር ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ማግኘት አለበት የሚለውን መርሕ በመጣሱ ራሱን ጥሎአል፣ ኀጢአትም ሠርቶአል ይሉ ነበር::

11፥8 *ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት … ዘርፌአቸዋለሁ፤* ቀደም ሲል ከተቋቋሙት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ርዳታን በነጻ ሲቀበል ነበር::

11፥9 *ሸክም፤* በሚያስፈልገው ነገር ባለዕዳ እንዳልሆነ ያመለክታል (የ2፥17 ማብ ይመ)፤ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነጻ ስጦታ እንደሆነ ያስተማረውን ትምህርት ያጸናል:: *ከመቄዶንያ የመጡ ወንድሞች፤* በዚያ አውራጃ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት (ሐሥ 18፥5) በተለይም ከፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን (ፊል 4፥15) የተላከውን ስጦታ ያመጡ ናቸው::

11፥12 *እኩል፤* ገንዘብን በሚመለከት ነው:: *ወደፊትም አደርጋለሁ፤* ጳውሎስ ወንጌልን ያለ ክፍያ እንዳይሰብክ የሚከለክለው ምንም ነገር የለም:: ያለ ክፍያ በመስበኩ ግን ተቃዋሚዎቹ እጅግ እንዲጠሉት አድርጎአል:: ጠላቶቹ ለጥቅም ይሰገበገቡ ስለ ነበር፣ ጳውሎስ ለትምህርቱ ገንዘብ ለመቀበል ፈቃደኛ ቢሆን ኖሮ እርሱን ለማጥመድ ይበልጥ በተሳካላቸው ነበር፤ ይህም ከእነርሱ በምንም እንዳይለይ ያደርገው ነበር::

11፥13 *የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋወጡ፤* ጳውሎስ እነዚህ፣ "ዋነኛ ሐዋርያት" (ቍ5) በመባል

ሐሰተኞች ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተ
ኞች ናቸው:: [14]ይህም የሚያስደንቅ ነገር
አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብር
ሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋው
ጣል:: [15]እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣ የጽ
ድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለ
ውጡ የሚያስገርም አይደለም፤ ፍጻሜአቸ
ውም እንደ ሥራቸው ይሆናል::

**ጳውሎስ በደረሰበት መከራ ይመካል**

[16]እንደ ገና ይህን እላለሁ፤ ማንም ሰው
እንደ ሞኝ አይቍጠረኝ፤ እናንተም የምት
ቈጥሩኝ ከሆነ እኔም በጥቂቱ እንድመካ
እንደ ሞኝ ተቀበሉኝ:: [17]እንደዚህ ልበ ሙሉ
ሆኜ የምናገረው እንደ ሞኝ እንጂ እንደ
ጌታ ፈቃድ አይደለም:: [18]ብዙዎች በዓለ
ማዊ ነገር ስለሚመኩ እኔም ደግሞ እመካ
ለሁ:: [19]እናንተም ብልሆች ስለ ሆናችሁ
ሞኞችን በደስታ ትታገሣላችሁ፤ [20]ማንም
ተነሥቶ ባሪያ ቢያደርጋችሁ፣ ቢበዘብዛችሁ፣
ለጥቅሙ ሲል ቢጠጋችሁ፣ ቢንቀባረርባችሁ
ወይም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገ
ሣላችሁ:: [21]እኛ ግን ለዚያ እጅግ ደካሞች
መሆናችንን እያፈርሁ እናገራለሁ::

ማንም በድፍረት በሚመካበት ነገር ሁሉ
እኔም ደፍሬ መመካት እንደምችል እንደ
ሞኝ እናገራለሁ:: [22]እነርሱ ዕብራውያን ናቸ
ውን? እኔም ነኝ፤ እስራኤላውያን ናቸውን?
እኔም ነኝ፤ የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔም
ነኝ:: [23]የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ
አበደ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤
ደግሞም ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ
ጊዜ ታስሬአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤
ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ:: [24]አይሁድ
ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ
ገርፈውኛል:: [25]ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድ
ቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤
ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤
አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአ
ለሁ፤ [26]ብዙ ጊዜ በጕዞ ተንከራትቻለሁ፤
ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴ
ዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ
አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣
ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወን
ድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር:: [27]ብዙ ጥሬ
አለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅ
ልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤
ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብ
ርድና በራቍትነት ተቈራምጃለሁ:: [28]ሌላ
ውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት ዕለት የሚያስ
ጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ
ነው:: [29]ደካማ ማን ነው? እኔስ አብሬ አል
ደክምምን? በኀጢአት የሚሰናከል ማን ነው?
እኔስ አልቈጭምን?

[30]መመካት ካለብኝ፣ ደካማነቴን በሚያ
ሳዩ ነገሮች እመካለሁ:: [31]ለዘላለም የተመሰ

11፥14 ማቴ4፥10
11፥15 ማቴ16፥27 ፊል3፥19
11፥16 ቍ1
11፥17 ቍ21፤1ቆሮ 7፥12:25
11፥18 ቍ21፤2ቆሮ 5፥16፤10፥4፤ፊል3፥ 3:4
11፥19 ቍ1፤1ቆሮ 4፥10
11፥20 ቍ1፤ገላ2፥4 ፤4፥9፤5፥1
11፥21 ቍ17:18፤ 2ቆሮ10፥1፥10፤ፊል 3፥4
11፥22 ሉቃ3፥8፤ ሮሜ9:4፤11፥1፤ፊል 3፥5
11፥23 ሐሥ16፥23 ፤ሮሜ8፥36፤1ቆሮ 3፥5፤15፥10፤2ቆሮ 6፥4:5
11፥24 ዘዳ25፥3
11፥25 ሐሥ14፥19 ፤16፥22፤27፥1-44
11፥26 ሐሥ20፥3፤ 21፥31፤ገላ2፥4
11፥27 ሐሥ18፥3፤ 1ቆሮ4፥11:12፤2ቆሮ 6፥5፤ቈላ1፥29
11፥28 1ቆሮ7፥17
11፥29 ማቴ5፥29፤ ሮሜ14፥1፤1ቆሮ2፥3
11፥30 ቍ16፤1ቆሮ 2፥3፤2ቆሮ12፥5:9፤ገላ 6፥14

የተጠሩትን ሰዎች እውነተኛውን ማንነታቸውን የሚሸፍኑ ሐሰተኞች ሐዋርያትና የሰይጣን አገልጋዮች (ቍ 14) መሆናቸውን ገልጾአል::

11፥14 *የብርሃን መልአክ ለመምሰል፤* እርሱ ግን በእርግጥ የጨለማው ገዥ ነው::

11፥16 *ማንም ሰው እንደ ሞኝ አይቍጠረኝ፤* የቍ 1 ማብ ይመ::

11፥18 *እመካለሁ፤* የሚመካ ስለ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ ባሕርይ በመናገሩ ነው::

11፥19 *ሞኞችን በደስታ ትታገሣላችሁ፤* በቍ 4 ላይ የጀመረውን ተግሣጽ እዚህም ላይ ተመሳሳይ በሆነ ምፀታዊ አነጋገር ይቀጥላል፤ በቍጥር 4 ላይ የተናገረው ሐሰተኛ ትምህርትን በትዕግሥት ለመቀበል ስለ ነበራቸው ዝግጁነት ነው፤ እዚህ ላይ የሚናገረው ደግሞ ራስ ወዳዶችና ትምክህተኞች በመሆናቸው ሞኞች የተባሉትን የሐሰተኞች መምህራንን አሳፋሪ ተግባር በትዕግሥት ለመቀበል ስላላቸው ፈቃደኝነት ነው::

11፥20 *ባሪያ ቢያደርጋችሁ፤* ከባድና ሰው ሠራሽ ሕግ በላያቸው በመጫን ነው (ከገላ 5፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: *ቢበዘብዛችሁ፤* ማር 12፥40 ይመ:: *ለጥቅሙ ሲል ቢጠጋችሁ፤* የቆሮንቶስ ሰዎች ክፉና ደጉን የመለየት ችሎታ ስለሌላቸው እንዲሁም በውጫዊ ነገሮች በብልጠት ንግግር በቀላሉ ለመታለል የተጋለጡ በመሆናቸው ነው:: *ቢንቀባረርባችሁ፤* በቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ ለመሠልጠን ሲል ነው (ከ1፥24 ጋር ያነጻጽሩ):: *ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ፤* እንዲገዙላቸው ለማድረግ ኀይል መጠቀማቸውን የሚያሳይ ነው::

11፥21 *እጅግ ደካሞች መሆናችንን፤* በጭካኔያቸውና በራስ ወዳድነታቸው ከሚታወቁት ከእነዚያ አስመሳዮች ጋር የጳውሎስ ተግባር ሲነጻጸር፣ ደካማ መስሎ ሊታይ ይችላል፤ እዚህ ላይ ግን የሚናገረው በምፀት ሳይሆን አይቀርም::

11፥22 *ዕብራውያን ... እስራኤላውያን ... የአብርሃም ዘር፤* እዚህ ላይ ሐሰተኞቹ ሐዋርያት የሚመኩባቸውን ነገሮች ስንመለከት፣ ከአሕዛብ ወገን ከሆኑ ክርስቲያኖች እንበልጣለን የሚሉ አይሁድ እንደሆኑ እንረዳለን:: በመሆኑም ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች የአይሁድን ልማድና ሥርዐት እንዲቀበሉ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ሳይሆኑ አይቀሩም:: የጳውሎስ አመለካከት ግን ከዚህ የተለየ ነበር (ሮሜ 2፥28-29፤ 1ቆሮ 12፥13፤ ገላ 3፥28-29፤ ኤፌ 2፥11-18፤ ቈላ 3፥11 ይመ):: ጳውሎስ ስለ ራሱ ማንነት የሚናገረውን በሐሥ 22፥3-5፤ 26፥ 4-5፤ ፊል 3፥5-6 ላይ ይመ::

11፥23 *የክርስቶስ አገልጋዮች፤* ሐሰተኞቹ መምህራን የክርስቶስ አገልጋዮች ነን ለሚሉት ነገር ቦታ መስጠቱ አይደለም:: ይልቁንም የአገልግሎቱን ሁኔታና ስለ አገልግሎቱ የተቀበለውን መከራ ስንመለከት ጳውሎስ ከማናቸውም ይበልጥ የክርስቶስ አገልጋይ እንደ ሆነ ግልጽ ነው:: *ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ፤* ከ4፥8-11 ጋር ያነጻጽሩ:: ጳውሎስ በእርግጥ ሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ነበር፤ ምክንያቱም በዚህ ቦታና ቀጥሎ ባሉት ቍጥሮች ላይ የዘረዘራቸው መከራዎች ለሕይወቱ እጅግ አሥጊ ነበሩ::

11፥24-25 *ጅራፍ ... ዱላ፤* እዚህ ላይ ስምንት ጊዜ እንደ ተደበደበ ተጠቅሶአል፤ አምስት ጊዜ በአይሁድ እጅ (ከዘዳ25፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሦስት ጊዜ በሮማውያን እጅ በዱላ (ሐሥ 16፥22-23 ይመ) ተደብድቦአል:: ጳውሎስ በዜግነቱ ሮማዊ በመሆኑ በዚህ ዐይነት እንዲቀጣ ሕጉ ባይፈቅድም፣ ሦስት ጊዜ በዱላ ተመቶአል (ከሐሥ16፥37-39፤ 22፥25-29 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥25 *በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤* በአይሁድ ልማድ መሠረት የሞት ቅጣት የሚፈጸመው በዚህ መንገድ ነበር (ከሐሥ 14፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ):: *የመርከብ አደጋ፤* በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ አንድ የመርከብ አደጋ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን እርሱም ይህ መልእክት ከተጻፈ በኋላ የተፈጸመ ነው (ሐሥ 27፥39-44):: እዚህ ላይ የተጠቀሱት ሦስቱ የመርከብ አደጋዎች የደረሱት በሐሥ 9፥30፤ 11፥25-26፤ 13፥14:13፤ 14፥25-26፤ 16፥11፤ 17፥14፤ 18፥18-19:21-22 ላይ በተገለጹት ጕዞዎች ላይ ሊሆን ይችላል:: *አንድ ሌሊትና ቀን፤* ከተጠቀሱት የመርከብ አደጋዎች በአንዱ ያጋጠመው ሁኔታ ሊሆን ይችላል::

11፥26 *ለ ... አደጋ፤* ጳውሎስ ቀደም ባሉት ቍጥሮች ላይ ከተዘረዘሩት መከራዎች በተጨማሪ አደጋና ችግር በተለያየ ጊዜ አጋጥሞት ነበር (የሐሥ 14፥24 ማብ ይመ)::

*11፥29፤* ጳውሎስ ራሱን ከደካሞች ጋር በመቍጠር የሌሎችን ድካም ይካፈል ነበር:: ደግሞም አንድ ሰው ኀጢአት ቢሠራ፣ እንዲህ በሠራው ሰው ላይ መቈጣት ብቻ ሳይሆን በደሉ የሚያስከትለው ውርደት ይሰማውና ኀጢአት የሠራውም ሰው በንስሓ እንዲመለስ ይመኝ ነበር::

11፥30 *ደካማነቴን በሚያሳዩ ነገሮች እመካለሁ፤* የራሱ ድካም እጅግ ታላቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲለማመድ መንገድ ይከፍትለታል፤ ስለዚህ እርሱ የሚመካው እንደ ሐሰተኞቹ ሐዋርያት ራሱ ባደረገው ሳይሆን ሙሉ በሙሉ እግዚ

ገነው የጌታ የኢየሱስ አምላክና አባት እን
ደማልዋሽ ያውቃል። 32ደማስቆ ሳለሁ ከን
ጉሥ አርስጦስዮስ በታች የሆነው ገዥ ሊያ
ሲዘኝ ፈልጎ፣ የደማስቆ ሰዎችን ከተማ
ያስጠብቅ ነበር። 33ነገር ግን በግንቡ መስ
ኮት በኩል በቅርጫት አውርደውኝ ከእጁ
አመለጥሁ።

## ጳውሎስ ያየው ራእይና የተሰጠው መውጊያ

12 በመመካት የሚገኝ ጥቅም ባይኖ
ርም፣ መመካት ካስፈለገ ከጌታ
ወደ ተቀበልሁት ራእይና መገለጥ አመራ
ለሁ። 2ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ
ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀ በክር
ስቶስ አንድ ሰው ዐውቃለሁ፤ የተነጠቀው
በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ አላው
ቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል። 3ይህ ሰው
በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ እኔ
አላውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል፤ 4እር
ሱም ወደ ገነት እንደ ተነጠቀ፣ በዚያም
በሰው አንደበት ሊገለጥ የማይችል፣ ሰውም
እንዲናገረው ያልተፈቀደለት ነገር ሰማ።
5እንደዚህ ስላለው ሰው እመካለሁ፤ ስለ ራሴ
ግን ከደካማነቴ በስተቀር አልመካም። 6መመ
ካት ብፈልግ እንኳ እንደ ሞኝ መቈጠር
የለብኝም፤ ምክንያቱም የምናገረው እውነት
ነው። ነገር ግን ማንም ስለ እኔ ከሚያየውና
ከሚሰማው በላይ እንዳይገምተኝ ከመመ
ካት እቈጠባለሁ።
7ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታ
በይ የሥጋዬ መውጊያ፣ እርሱም የሚያሠ
ቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ። 8ይህ
ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን ሦስት
ጊዜ ለመንሁት፤ 9እርሱ ግን፣ "ጸጋዬ ይበቃ
ሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ
ነውና" አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ
ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድ
ካሜ እመካለሁ። 10ስለ ክርስቶስ በድካም፣
በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭንቀት
ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያን ጊዜ
ብርቱ ነኝና።

## ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረው ጭንቀት

11በመመካቴ ሞኝ ሆኛለሁ፤ ለዚህም ያበ
ቃችሁኝ እናንተ ናችሁ፤ ስለ እኔ መመስ
ከር የሚገባችሁ እናንተ ነበራችሁ። ደግሞም
እኔ ከምንም የማልቈጠር ብሆንም፣ "ታላ
ላቅ ሐዋርያት" ከሚባሉት በምንም አላን
ስም። 12የእውነተኛ ሐዋርያ ምልክቶች
በመካከላችሁ ተደርገዋል፤ እነርሱም በትዕ
ግሥት መጽናት፣ ምልክቶች፣ ድንቅ ነገሮ
ችና ታምራት ናቸው። 13በእናንተ ላይ ሸክም
ካለመሆኔ በቀር፣ ከሌሎች አብያተ ክርስ
ቲያናት በምን አነሳችሁ? ይህን በደሌን
ይቅር በሉኝ።
14ወደ እናንተ ለመምጣት ስዘጋጅ ይህ
ሦስተኛዬ ነው፤ ስመጣ በምንም ነገር ሸክም
አልሆንባችሁም፤ እኔ እናንተን እንጂ ከእና
ንተ ምንም አልፈልግምና፤ ደግሞም ወላ
ጆች ለልጆች ገንዘብ ያከማቻሉ እንጂ ልጆች

11፥31 ቍ11፥ሮሜ 1፥9፡25፤9፥5
11፥32 ሐሥ9፥24
11፥33 ሐሥ9፥25
12፥1 ቍ5፡7፡9፤ 1ቆሮ2፥10፤2ቆሮ 11፥16፡30
12፥2 ቍ4፡ሐሥ8፥ 39፤ሮሜ16፥3፤2ቆሮ 11፥11፤ኤፌ4፥10
12፥4 ቍ2፤ሉቃ 23፥43፤ራእ2፥7
12፥5 ቍ9፡10፤ 1ቆሮ2፥3
12፥6 ቍ11፤2ቆሮ 10፥8፤11፥16
12፥7 ቍ1፤ዘኍ33፥ 55፤ማቴ4፥10፤1ቆሮ 2፥10
12፥8 ማቴ26፥39፡ 44
12፥9 1ነገ19፥12፤ ሮሜ3፥24፤1ቆሮ 2፥3፤ፊል4፥13
12፥10 ማቴ5፥12፤ 2ቆሮ6፥4፤13፥4፤2ተሰ 1፥4
12፥11 1ቆሮ15፥9፡ 10፤2ቆሮ11፥1፡5
12፥12 ዮሐ4፥48
12፥13 ቍ14፤1ቆሮ 9፥12፡18፤2ቆሮ11፥7
12፥14 ምሳ19፥14፤ 1ቆሮ4፥14፡15፤2ቆሮ1 3፥1

አብሔር ባደረገው ነገር ነው።

11፥32 *ከንጉሥ አርስጦስዮስ፤* ራብዓዊው አርስጦስዮስ ነው፤ እርሱም ከ9 ዓ.ቅ.ክ እስከ 40ዓ.ም ገደማ የናባቲያን ዐረቦችን የገዛው የሄሮድስ አንቲጳስ ዐማች ነበር። የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ካሊጉላ በአንድ ወቅት ግዛቱ የነበረችውን ደማስቆን ለአርስጦስዮስ ሳይሰጠው አይቀርም።

12፥1 *ራእይና መገለጥ፤* የጳውሎስ ተቃዋሚዎች የሚያስተምሩትን ትምህርት በራእይና በመገለጥ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ተቀብለናል ብለው በሐሰት ቢናገሩም፣ ጳውሎስ ግን በእርግጥ በዚህ መንገድ ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበለ ይናገራል። ይህንንም እዚህ ላይ የጠቀሰው በመንፈስ ወደ ሰማይ ቢወሰድም እንዳይታበይ የተሰጠውን ሥቃይ (ቍ7) ለመግለጽ ነው፤ ይህም "የጸጋ ሁሉ አምላክ" (1ጴጥ 5፥10) በሆነው በእግዚአብሔር እንጂ በራሱ እንዳይመካ ነው።

12፥2-4 *እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀ ... ወደ ገነት እንደ ተነጠቀ፤* ጳውሎስ በዚህ ድንቅ በሆነ ሁኔታ ስለ መነጠቁ አይጠራጠርም፤ ይሁን እንጂ የተነጠቀው ከነሥጋው ይሁን ወይም አይሁን እርግጠኛ አይደለም። ሦስተኛው ሰማይ ከምድር ከባቢ አየርና ከጠፈር በላይ ያለ የእግዚአብሔር መኖሪያ ነው። ከሙታን የተነሣውና የከበረው ጌታ፣ "በሰማያት ያለፈ" (ዕብ 4፥14)፣ "ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣና" (ኤፌ4፥10) "ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ" (ዕብ7፥26) ነው። "ገነት" የሚለው ቃል ሦስተኛ ሰማይ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ በሞት የተለዩ አማኞች፣ "ከጌታ ጋር የሚሆኑበት" ስፍራ ነው (5፥8፤ "ከክርስቶስ" ፊል 1፥23 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ የሰማውና በአንደበቱ ሊገልጸው ያልቻለው ነገር ምን እንደ ሆነ ማወቅ አንችልም፤ ምክንያቱም እርሱ ራሱ እንዲናገር አልተፈቀደለትም። ይህ ድንቅ የሆነ መነጠቅ ለሐዋርያዊ አገልግሎቱ ከፍተኛ ብርታት ስለ ሰጠው፣ የደረሰበትን ከባድና ጽኑ መከራ ሁሉ በትዕግሥት ችሎ እንዲያልፍ ረድቶታል። ከዚህም በላይ ይህ ልምምድ ከራሱ የመነጨ ስላልሆነ በራሱ የሚያስመካው አንዳች ነገር የለውም (ቍ5-6)።

12፥5 *እንደዚህ ስላለው ሰው እመካለሁ፤* አንዳንዶች ይህ፣ "እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ" (ቍ2) የተባለው ሰው ጳውሎስ አይደለም፤ ደግሞም ጳውሎስ እዚህ ላይ አጥብቆ ሊናገር የፈለገው እርሱ የሚመካው ባገኘው ታላቅ ልምምድ ሳይሆን በድካሙ ነው ይላሉ።

12፥7 *የሥጋዬ መውጊያ፤* ይህ ብርቱ ሥቃይ ምን እንደ ሆነ በትክክል አይታወቅም። *የሰይጣን መልእክተኛ፤* ለጳውሎስ የተሰጠውን መውጊያ የሚያብራራ ተጨማሪ መግለጫ ነው (ከ1ቆሮ 5፥5፤ 11፥30፤ 1ጢሞ 1፥20 ጋር ያነጻጽሩ፤ ኢዮ 2፥10 ይመ)።

12፥9 *ጸጋዬ ይበቃሃል፤* ለጳውሎስ የተሰጠውን መውጊያ ከማስወገድ የተሻለ መፍትሔ ነው። የሰው ድካም የመለኮት ኀይል እንዲገለጥ ያደርጋል።

*12፥10፤* ከኤፌ 3፥16፤ ፊል 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ።

12፥11 *ሞኝ ሆኛለሁ፤* የ11፥1 ማብ ይመ። *ለዚህም ያበቃችሁኝ እናንተ ናችሁ፤* ጳውሎስ ስለ ራሱ እንዲናገር ያስገደዱት የቆሮንቶስ ሰዎች ናቸው፤ ምክንያቱም እነርሱ በመካከላቸው ሠርገው የገቡትን፣ የጳውሎስን ሐዋርያዊ ሥልጣን የሚቃናቀኑትንና "ዋነኛ ሐዋርያት" ተብለው የተጠሩትን ሰዎች በደስታ ተቀብለዋቸው ነበር።

12፥12 *የእውነተኛ ሐዋርያ ምልክቶች፤* በመካከላቸው ታላላቅ ስጦታዎችና ድንቅ ነገሮች ተገልጠው ነበር። ሐሰተኞቹ መምህራን ግን ወደ እነርሱ የመጡት ያለ እነዚህ ምልክቶች እንደ ሆነ መገመት ይቻላል (ከዕብ 2፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)።

12፥13 *በእናንተ ላይ ሸክም ካለመሆኔ በቀር፤* የ11፥9 ማብ ይመ። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ወንጌልን ሲሰብክ ክፍያ ለመቀበል አለመፈለጉን፣ ተቃዋሚዎቹ መጥፎ ትርጒም ሰጥተውታል (የ11፥7፡11 ማብ ይመ)። እነዚህ ያገኙትን ሁሉ የሚያግበሰብሱት ሰዎች የቆሮንቶስን አማኞች የበደለው ራሱ ጳውሎስ ነው እያሉ ያስወሩ ነበር። *ይህን በደሌን ይቅር በሉኝ፤* በ11፥7-12 ላይ የጀመረውን ንግግር ሲቀጥል የተጠቀመበት ምፀታዊ አነጋገር ነው።

12፥14 *ሦስተኛዬ፤* የ2፥1 ማብ ይመ። *ሸክም አልሆንባችሁም፤* በተለይ በዚህኛው ጒብኝቱ ይህን የተናገረው፣ "ዋነኛ ሐዋርያት" የተባሉትን ሰዎች ሐሰተኛነትና ስስት ይፋ ለማድረግ ነው (11፥12 ይመ)። *ልጆች፤* ጳውሎስ መንፈሳዊ አባታቸው ነው (ከ 6፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

ለወላጆች አያከማቹም:: 15እኔ ግን ስለ እና
ንተ ያለኝን ሁሉ ራሴንም ጭምር ብሰጥ
ደስ ይለኛል፤ ታዲያ እኔ የምወዳችሁ ይህን
ያህል ከሆነ፣ እናንተ የምትወዱኝ በጥቂቱ
ነውን? 16የሆነው ሆኖ ሸክም አልሆንሁባች
ሁም፤ ነገር ግን በተንኰልና በዘዴ ያጠመ
ድኋችሁ ሳይመስላችሁ አልቀረም! 17ለመ
ሆኑ ወደ እናንተ በላክኋቸው ሰዎች አማካ
ይነት በአንዱ እንኳ በዘበዝኋችሁን? 18ቲቶ
ወደ እናንተ እንዲመጣ ለመንሁት፤ ወንድ
ማችንንም ከእርሱ ጋር ላክሁት:: ቲቶ በዘ
በዛችሁን? ከእርሱ ጋር በአንድ መንፈስ
አልተመላለስንምን? አካሄዳችንስ አንድ አል
ነበረምን?
19እስከ አሁን ድረስ በእናንተ ፊት ራሳ
ችንን ስንከላከል የኖርን ይመስላችኋልን?
በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንናገራ
ለን፤ ደግሞም ወዳጆች ሆይ፤ ይህን ሁሉ
የምናደርገው እናንተን ለማነጽ ነው:: 20ወደ
እናንተ በምመጣበት ጊዜ፣ እኔ እንደምፈ
ልገው ሆናችሁ ላላገኛችሁ እችላለሁ ወይም
እናንተ እንደምትፈልጉኝ ሆኜ ላታገኙኝ
ትችላላችሁ ብዬ እፈራለሁ፤ ምናልባትም
በመካከላችሁ ጥል፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ አድመ
ኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ሐሜት፣ እብሪትና
ሁከት ይኖራል ብዬ እሠጋለሁ:: 21ዳግመ
ኛም ስመጣ አምላኬ በእናንተ ፊት ያዋር
ደኝ ይሆን ብዬ እፈራለሁ፤ ይኸውም ብዙ
ዎች ከዚህ በፊት ስለሠሩት ኀጢአትና ስለ
ፈጸሙትም ርኵሰት፣ ዝሙትና መዳራት
ንስሓ ሳይገቡ ቀርተው እንዳላዝን ነው::

## የመጨረሻ ምክር

13 ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሦስተኛዬ
መሆኑ ነው፤ "ማንኛውም ነገር በሁ
ለት ወይም በሦስት ምስክር ይጸናል::"
2በሁለተኛው ጕብኝቴ እናንተ ዘንድ በነበ
ርሁበት ጊዜ አስጠንቅቄአችሁ ነበር፤ አሁንም
በሩቅ ሆኜ እንደ ገና አስጠነቅቃችኋለሁ፤
ወደ እናንተም ተመልሼ ስመጣ ከዚህ በፊት
ኀጢአት ለሠሩትም ሆነ ለሌሎች አልራራ
ላቸውም፤ 3ይህም የሚሆነው ክርስቶስ በእኔ
አድሮ እንደሚናገር ማስረጃ በመፈለጋችሁ
ነው:: እርሱም በመካከላችሁ ብርቱ እንጂ
ደካማ አልነበረም:: 4የተሰቀለው በድካም ቢሆ
ንም፣ በእግዚአብሔር ኀይል ሕያው ሆኖ ይኖ
ራል:: እኛም በእርሱ ደካሞች ብንሆንም፣
እናንተን ለማገልገል ግን በእግዚአብሔር ኀይል
ከእርሱ ጋር ሕያዋን ሆነን እንኖራለን::
5በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳች
ሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ:: ፈር የወጣ
ችሁ ካልሆነ በስተቀር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በው
ስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን? 6እኛ ግን
ብቁ መሆናችንን እንደምትገነዘቡ ተስፋ
አደርጋለሁ:: 7አሁንም ምንም ክፉ ነገር እን
ዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፤
የምንጸልየውም እኛ ብቁዎች እንደ ሆንን
ሰዎች እንዲያዩልን አይደለም፤ ነገር ግን
እኛ ምንም እንኳ ብቁዎች ባንሆንም እናንተ
መልካም የሆነውን ነገር እንድታደርጉ
ነው:: 8ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ
ምንም ማድረግ አንችልምና:: 9እኛ ደካሞች
ስንሆን፣ እናንተ ግን ብርቱዎች ስትሆኑ
ደስ ይለናል፤ ጸሎታችንም እናንተ ፍጹማን
እንድትሆኑ ነው:: 10ከእናንተ ርቄ ሳለሁ
እነዚህን ነገሮች የምጽፍላችሁ ወደ እናንተ
በምመጣበት ጊዜ ሥልጣኔን በኀይል እንዳ
ልጠቀም ነው፤ ጌታም ይህን ሥልጣን የሰጠኝ
እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይ
ደለም::

12፥15 2ቆሮ11፥11 ፤ፊል2፥17፤1ተሰ2፥8
12፥16 2ቆሮ11፥9
12፥18 2ቆሮ2፥13፤ 8፥6:16:18
12፥19 ሮሜ9፥11 14፥19፤1ቆሮ10፥14፤ 2ቆሮ10፥8
12፥20ሮሜ1፥29:30 ፤1ቆሮ1፥11፤3፥3፤4፥1 8፤21፤14፥33፤2ቆሮ 2፥1-4፤ገላ5፥20
12፥21 1ቆሮ6፥18 ፤2ቆሮ2፥1:4፤13፥2
13፥1 ዘዳ19፥15፤ ማቴ18፥16፤2ቆሮ 12፥14
13፥2 ቊ10፤2ቆሮ 1፥23፤12፥21
13፥3 ማቴ10፥20 ፤1ቆሮ5፥4
13፥4 ቊ9፤ሮሜ 1፥4፤6፥4፤6፥5፤1ቆሮ1 ፥25፤2፥3፤6፥14፤ፊል2 ፥7:8፤1ጴጥ3፥18
13፥5 ሰቆ3፥40፤ዮሐ 6፥6፤ሮሜ8፥10፤1ቆሮ 11፥28
13፥9 ቊ11፤1ቆሮ 2፥3፤2ቆሮ2፥3፤4፥12፤ ኤፌ4፥13
13፥10 2ቆሮ1፥23 ፤10፥8

*12፥15፤* የአባትነት ፍቅሩን የገለጸላቸው ያለውን ገንዘብ ሁሉ ለእነርሱ ለመቸር ዝግጁ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱን ስለ እነርሱ በደስታ አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑም ነው::

12፥16 *በዘዴ ያጠመድኋችሁ፤* ሐሰተኞቹ ሐዋርያት የጳውሎስን ስም ለማጥፋት የተናገሩትን በአግቦ መልክ ማንጸባረቁ ነው፤ ይኸውም በኢየሩሳሌም በሚገኙ ችግረኞች ክርስቲያኖች ስም የርዳታ ገንዘብ እያሰባሰበ ወደ ገዛ ኪሱ ይከታል እንጂ፣ የተሰበሰበው ገንዘብ ለችግረኞቹ አይደርስም ይሉት ነበር (ቍ 17):: እንግዲህ ሸክም ላለመሆን መፈለጉ አያስደንቅም:: እውነቱ ግን እንደ፣ "ጽድቅ አገልጋዮች" አድርገው ራሳቸውን የሚለዋውጡት እነዚሁ፣ "አታላዮች" ሠራተኞች ናቸው (11፥13-14):: ጳውሎስ በአካሄዱም በኅሊናውም እንከን የለሽ እንደ ሆነ የቆሮንቶስ ሰዎች በሚገባ የሚያውቁት ጕዳይ ነበር::

12፥18 *ቲቶ ... ወንድማችንንም፤* የ 8፥6:16:18-23 ማብ *ይመ*::

12፥19 *በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንናገራለን፤* ጳውሎስ ስለ ራሱ የተናገረው በሰዎች ዘንድ ክብርንና ዝናን ለማትረፍ አልነበረም (ከ1ቆሮ 4፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ):: እርሱ የቆመው በእግዚአብሔር ፊት ነው፤ በእግዚአብሔር ፊት የቆመውም በክርስቶስ ነው:: እርሱ የሚያስበው ለራሱ ሳይሆን ወዳጆቹ ለሆኑት ለቆሮንቶስ ሰዎች ነው፤ እነርሱም የሚበረቱት በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሲቆሙ ነው:: በአገልግሎቱ መከራ የሚቀበለውም ለዚሁ ዐላማ ነበር (ከ10፥8 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥2 *ለሌሎች አልራራላቸውም፤* ጳውሎስ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ፣ በሥርዐት በማይመላለሱት ላይ ጠንካራ እርምጃ ከመውሰድ አይመለስም::

13፥3 *ክርስቶስ በእኔ አድሮ እንደሚናገር ማስረጃ በመፈለጋችሁ፤* የ10፥10 ማብ ይመ:: ሐሳባቸውን ካልቀየሩ በስተቀር ወደ እነርሱ ሲመጣ በቂ ማስረጃ ይሰጣቸዋል:: *እርሱም ... ደካማ አልነበረም፤* በጳውሎስ ላይ ማመፅ ማለት እርሱን ሐዋርያ አድርጎ በሾመው በክርስቶስ ላይ ማመፅ ማለት ነው:: የሐዋርያው ሥልጣን የጌታ ሥልጣን ነው:: ጳውሎስ ደካማ እንደ ሆነ የሚያስብ ሰው በሐዋርያው አማካይነት የሚናገረው ክርስቶስ ደካማ ሳይሆን ብርቱ መሆኑን ይገነዘባል::

13፥4 *በእግዚአብሔር ኀይል ከእርሱ ጋር ሕያዋን ሆነን እንኖራለን፤* ጳውሎስ ይህንን የተናገረው ስለተሰጠው ሐዋርያዊ ሥልጣን ነው፤ ደግሞም ይህን ሥልጣን የሚቃወም ሰው በሚቀጣበት ጊዜ መለኮታዊ ኀይል ይገለጣል::

13፥5 *ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁንም ፈትኑ፤* በሐሰተኞች ሐዋርያት ተገፋፍተው ክርስቶስ በእርሱ አማካይነት እንደሚናገር (ቍ 3) ለማረጋገጥ ማስረጃ ከመፈለግ ይልቅ የገዛ ልባቸውን መመርመር ይገባቸዋል::

13፥7 *መልካም የሆነውን ነገር እንድታደርጉ፤* ይህ ከሆነ ጳውሎስ ወደ እነርሱ ሲመጣ የቅጣት እርምጃ በመውሰድ ሥልጣን እንዳለው ማሳየት አያስፈልገውም::

13፥8 *በእውነት ... ላይ ምንም ማድረግ አንችልምና፤* ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣኑን የሚጠቀመው በእውነት መንገድ ብቻ ነው:: ስለዚህ ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ የቆሮንቶስ ሰዎች እውነቱን ተቀብለው ካገኛቸው የሥነ ሥርዐት እርምጃ መውሰድ አያስፈልገውም::

13፥9 *ደካሞች፤* ሐዋርያዊ ኀይሉን ለመግለጽ ማስረጃ ማቅረብ እንዳያስፈልገው ነው:: *ብርቱ፤* በእውነት ነው::

*13፥11-14፤* እነዚህ የማጠቃለያ ምክርና የስላምታ ቃላት፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የሚሰጣቸውን ምክር እንደሚቀበሉ ያሳያሉ::

## የመጨረሻ ሰላምታ

[11]በተረፈ ወንድሞች ሆይ፤ ደኅና ሁኑ።
ፍጹማን ሆኑ፤ ምክሬን ስሙ፤ አንድ ሐሳብ
ይኑራችሁ፤ በሰላምም ኑሩ። የፍቅርና የሰላ
ምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል። [12]በተ
ቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰ
ጣጡ። [13]ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላ
ችኋል።
[14]የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚ
አብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት
ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

13፥11 ማር9፥50
፤ሮሜ15፥33፤ኤፌ
6፥23፤1ተሰ4፥1፤2ተሰ
3፥1፤1ዮሐ4፥16
13፥12 ሮሜ16፥16
13፥13 ፊል4፥22
13፥14 ሮሜ5፥5፤
16፥20፤2ቆሮ8፥9፤ፊል
2፥1፤ይሁ21

13፥11 *የሰላምም አምላክ፤* የ1ተሰ 5፥23 ማብ ይመ።

13፥12 *አሳሳም፤* የመተማመንና የፍቅር ምልክት ሲሆን፣ በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች አሁንም የተለመደ ነው። የክር ስቲያኖች አሳሳም የተቀደሰ መሆን አለበት፤ ደግሞም ሰላምታ ሁሉ በክርስቶስ ስም የሚቀርብ ንጹሕና ቅን መሆን ይኖርበታል (1፥2 ይመ)።

*13፥14፤* ቃለ ቡራኬው ሥላሴያዊ ቅርጽ ያለው ሲሆን፣ ከጥንት ጀምሮ በክርስትና አምልኮ ውስጥ ስፍራ ተሰጥቶት ቈይ ቶአል። ይህም የቅድስት ሥላሴ ምስጢር የሚታወቀው በአ እምሮ ወይም በፍልስፍና ሳይሆን በክርስቲያናዊ ልምምድ መሆ ኑን ያስገነዝበናል፤ በዚህም አንድ አማኝ ጸጋ፣ ፍቅርና ኅብረት እንዲያው የሚፈስለት ከአንዱ እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንደሆነ ያውቃል።